# አዲስ ዘመን

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 271 ሰኔ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!











ፎቶ- ገባቦ ገብሬ

# የ2015 ረቂቅ በጀት

## - ስመደበኛና ካፒታል ወጪ 563 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር መመደቡን አመላክቷል

## - የወጪ ትኩረት በዕዳ ክፍያ፣በሰብዓዊ ዕርዳታ፣ በመልሶ ግንባታና የሀገርን ደህንነት ማስጠበቅ ላይ ይሆናል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ረቂቅ በጀት ለመደበኛ ወጪ 345 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ፣ ለካፒታል ወጪ 218 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር መመደቡንና፤ ለክልል መንግሥታት ድጋፍ 209 ነጥብ አራት ቢሊዮን እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 14 ቢሊዮን ብር መቅረቡን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የመንግሥት ወጪ ትኩረት በዕዳ ክፍያ፣በሰብዓዊ ዕርዳታ፣ በመልሶ ግንባታና የሀገርን ደህንነት የማስጠበቅ አቅም ላይ እንደሚሆን ተገልጿል።

የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሺዴ ትናንትና ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንደኛ ዓመት የስራ ዘመን 11 መደበኛ ስብሰባውን ሲያደርግ የፌዴራል መንግሥት የ2015 በጀት ዓመት ረቂቅ በጀት ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በወቅቱ ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ ለ2015 በጀት ዓመት የቀረበው 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር ረቂቅ በጀት በ2014 በጀት ዓመት አጠቃላይ ከፀደቀው ጭማሪ በጀት አንጻር የ16 ነጥብ 6 በመቶ ጭማሪ አለው።

ረቂቅ በጀቱም የሀገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ትንበያን መሠረት ያደረገ ነው። የበጀቱ መደበኛ ወጪ አብዛኛው ለዕዳ ክፍያ፣ የሀገር ደህንነትን ለማስጠበቅ፣ በጦርነትና በአየር ንብረት ለውጥ የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የሚውል የዕለት ዕርዳታ፣ ለአፈር ማዳበሪያና ስንዴ ድጎማ ትኩረት ሰጥቷል ብለዋል።

ለዕዳ ክፍያ ፣ ለመከላከያ፣ ለዕለት ዕርዳታና ለማዳበሪያ ድጎማ የተደለደለው በጀት 239 ቢሊዮን ብር መሆኑን ገልጸዋል።

አጠቃላይ ተደግፎ ከቀረበው የፌዴራል መደበኛና ካፒታል በጀት ውስጥ 37 ነጥብ አምስት በመቶው ለመንገድ ፣ ለትምህርት፣ ለውሃና ኢነርጂ፣ ለጤና፣ ለከተማ ልማትና የግብርና ዘርፎች የተመደበ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለዘርፎቹ የተመደበው ረቂቅ በጀት ከ2014 በጀት


የ2015 ረቂቅ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










# በቤኒሻንጉል ክልል በተወሰደው ሕግ የማስከበር ዘመቻ በክልሉ አንጻራዊ ሰላም መስፈኑ ተገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡ በቤኒሻንጉል ክልል በተወሰደው ሕግ የማስከበር ዘመቻ በክልሉ አንጻራዊ ሰላም መስፈኑ የክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዮት አልቦሮ አስታወቁ። በአሁኑ ጊዜ ወደ ጫካ የሚወስድ የጉሙዝ ሕዝብ ጥያቄ አይኖርም ሲሉ አቶ አብዮት አልቦሮ ተናግረዋል።

አቶ አብዮት አልቦሮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ቀደም ሲል በኢሕአዴግ የሕወሓት መራሹ ዘመነ መንግሥት ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ያለው የቤኒሻንጉል ክልልን “ታዳጊ ክልል” በማለት የቤኒሻንጉል ክልልን ከፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከመግፋት በተጨማሪ በክልሉ የሞግዚት አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የክልሉን ሀብት ሲዘርፍ ቆይቷል።

ነገር ግን እንደ ሀገር በሀገሪቱ ለውጥ ዛሬ ላይ ክልሉ የራሱን ሀብት ከዝርፊያ ለማዳን ራሱን በራሱ ከማስተዳደር አልፎ በፌዴራል መንግሥት ውሳኔዎች የራሱን ድርሻ እያበረከተ ይገኛል።ይሁን እንጂ የክልሉ ለውጥ የክልሉን ሀብት ሲዘርፍ ለነበሩ የማይዋጥላቸው በመሆኑ ተላላኪ ኃይላትን በማደራጀት ቢሳካላቸው ሀገሪቱን ወደኋላ ለመመለስ ካልሆነ ግን ታላቁ የህዳሴ ግድብ እንቅስቃሴ ለማስተጓጎል ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።



አቶ አብዮት አልቦሮ

በተለይ ራሱን የጉሙዝ ሕዝብ ዴሞክራሲ ንቅናቄ(ጉሕዴን) ብሎ የሚጠራ ቡድን በመጀመሪያ በአገሪቱ ውስጥ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመታገል ሲንቀሳቀስ ቆይቶ በኋላ ላይ የትጥቅ ትግል በመምረጥ ወደ ጫካ ማምራቱን የጠቀሱት አቶ አብዮት፣ ከዚህ አንጻር የተላላኪነቱን አጀንዳ ያልተገነዘቡ የጉመዝ ወጣቶች በመመልመል ከሱዳን ጋር በመሆን ለወጣቶቹ ወታደራዊ ሥልጠናና ቁሳዊ ድጋፍ በማድረግ በክልሉ ብሎም በአገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርስ መቆየቱን ተናግረዋል።

ቡድኑ የህዳሴ ግድብ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ የግንባታ እቃዎች ወደዚያ እንዳያልፉ ፈንጂዎችን በመንገድ ላይ በመጥመድ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን ያወሱት ኃላፊው፣ በክልሉ የፀጥታ ሥራ ላይ የተሰማሩ የመከላከያ፣ የፌዴራልና የክልሉ ፀጥታ አካላት ላይ በተለያዩ ጊዜያት በደፈጣ ጥቃት ለማድረስ ሙከራ ማድረጉንም አክለው ገልጸዋል።

የጉሕዴንና የቤኒሻንጉል ነጻ አውጪ ታጣቂዎች በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች በማፈናቀል ያደረሱት ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች እንደ ቀላል የሚነገር እንዳልሆነ የተናገሩት አቶ አብዮት፣ ሆኖም ግን


በቤኒሻንጉል ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ- አዩብ ተፈሪ

አቶ ለሜሳ ቱሉ

# ዋጋ ማስተካከያው በነዳጅ ላይ የሚፈጸመውን ሕገ ወጥ ንግድን እንደሚያስቀም ባለስልጣኑ ገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በሐምሌ ወር የሚደረገው የታለመለት የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ በነዳጅ ላይ ሲፈጸም የነበረውን ሕገ ወጥ ንግድን እና ብክነትን ማስቀረት የሚችል መሆኑን የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን አስታወቀ።

በባለስልጣኑ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ስታንዳርድ ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ ቱሉ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያው በነዳጅ ላይ የሚፈጸመውን ሕገ ወጥ ንግድን ማስቀም ያስችላል።


ዋጋ ማስተካከያው በነዳጅ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## የሕወሓት የሽብር ቡድንን ሴራ በተገኘው ዓለም አቀፍ መድረክ ማጋለጥ ይገባል ተባለ


ገጽ 4



አቶ ገረሙ ኦሊቃ

# ከፍተኛ ዝናብ በሚዘንብባቸው አካባቢዎች ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የኦሮሚያ ክልል አሳሰበ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ ክረምት ከፍተኛ ዝናብ መጠን በሚጥልባቸው አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች አስፈላጊውን ቅድመ አደጋ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ኦሮሚያ አደጋ ሥጋት አመራር (ቡሳ ጎኖፋ ) አስታወቀ። በአንዳንድ ኦሮሚያ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊጥል እንደሚችል የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ተንብየዋል ።

ኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ገረሙ ኦሊቃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ቡሳ ጎኖፋ በክልሉ የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመከላከል እና በአደጋ ጊዜና ከአደጋ በኋላ መልሶ ማቋቋም ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል።

እስከ አሁን ድረስ በተሠራው ሥራ በድርቅ ጉዳት ለደረሰባቸው ስምንት ዞኖች ከኅብረተሰቡ ጋር በመሆን የሰው ሕይወትን ማዳን ያስቻለ ሥራ ተከናውኗል። በዘንድሮ ክረምትም ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚዘንብባቸው የክልሉ አካባቢዎችም አደጋ ለመቀነስ አስፈላጊውን የቅድመ አደጋ ሥራዎች በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ከሀገር አቀፍ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ በተገኘው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት የዘንድሮ ክረምት በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ የዝናብ መጠን ሊያስተናግዱ እንደሚችሉ አመላክተዋል ። ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በሚዘንብባቸው አካባቢዎች ኅብረተሰቡ ቅድመ አደጋ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ምክትል ኮሚሽነሩ አሳስበዋል።

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለጻ ክብደቱ ይለያይ እንጂ የክረምት ዝናብ በሚያገኙ ሁሉም አካባቢዎች አደጋ ሊከሰት ስለሚችል ኅብረተሰቡ ራሱን ለመከላከል የሚያስችል ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል ። በስምጥ ሸለቆ ፤በወንዞችና ሐይቆች አካባቢ የሚኖሩ ለጊዜው ከአካባቢው ርቀው በመቆየት ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸው ገልጸዋል ።

አዋሽ ወንዝ ተፋሰስ የሚነካቸው ኦሮሚያ ዞኖች ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ምስራቅ ሸዋ፣ አርሲና ፊንፊኔ ዙሪያ የሚገኙ ኦሮሚያ ልዩ ዞኖች የሚገኙ 15 ወረዳዎች አስፈላጊውን ቅድመ አደጋ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ምዕራብ ጉጂ ከአበያ ሐይቅ ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋና ሆሮ ጉዱሩ ከፍተኛ ዝናብ ሊጥል እንደሚችልና የመሬት መንሸራተት አደጋም ሊከሰት እንደሚችል አሳስበዋል።

ከአዋሽ ወንዝ ጋር በተያያዘ በየዓመቱ የሚመላለሰውን አደጋ በዘላቂ ለመፍታት አለመቻሉ እንደ አንድ ችግር አንስተዋል። ኅብረተሰቡም ቅድመ አደጋ መረጃዎችን ለመጠቀም ያለው ፍላጎት ውስን መሆን ለአደጋ መከላከል ሥራዎች እንቅፋት መሆኑን አያይዘው ገልጸዋል ።

የክልሉ መንግሥትም ከኅብረተሰቡና ከግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር በመሆን በድርቅ ለተጎዱ ለሶስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሰዎች የሚደረገ ድጋፍ እንደሚቀጥል ገልጸዋል። እስከ አሁን በተደረገው ድጋፍ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል እህል እህልና 77 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍ በማድረግ የሰውን ሕይወት ማዳን ተችሏል። እስከ አሁን ድረስ ተቆራርጦ በዘነበው ዝናብ ለከብቶች ምግብ የተሻለ ቢሆንም ለሰው ልጅ መፍትሔ ለመሆን ጊዜ ይወስዳል ብለዋል።

ኅብረተሰቡ ቅድመ አደጋ መረጃዎችን በመቀበል ቅድመ አደጋ ዝግጅት በማድረግ፣ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት አንድ ላይ ሆኖ አደጋን በመከላከል የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ምክትል ኮሚሽነሩ ጥሪ አቅርበዋል ።




# የጤና ሚኒስቴር ለትግራይ ክልል የሚያስፈልጉ መድኃኒት እና የሕክምና ቁሳቁሶች መቅረብ መቀጠላቸውን አስታወቀ

አዲስ አበባ፣ የኢፌዴሪ የጤና ሚኒስቴር ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ለትግራይ ክልል የተቀናጀ የጤና እና የስነ ምግብ አገልግሎት ማቅረብ መቀጠሉን አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ ከኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ጋር በመሆን ዓለም አቀፍ ተቋማትን በማስተባበር አስፈላጊ የጤና ግብዓቶች ለክልሉ እየቀረቡ ነው ብሏል።

ለአብነትም ባለፉት አምስት ወራት ብቻ 45 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ መድኃኒቶች እና ሌሎች የሕክምና ቁሳቁሶች ለክልሉ ተልኳል ብሏል።

በተጨማሪም የዓለም ጤና ድርጅት ለ1 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሰዎች ለሶስት ወራት የሚያገለግል የሕክምና ቁሳቁሶች እና የተመጣጠነ ምግብ ወደ ክልሉ መግባቱን ነው የጠቆመው።

እንደዚሁም 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ለመሠረታዊ ጤና አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች እና ከ64 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ የኮሌራ እና ወባ በሽታዎች መከላከያዎችን ጨምሮ የተለያዩ የተመጣጠኑ ምግቦች ቀርበዋል ብለዋል።

በዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበር በኩል ለግማሽ ሚሊዮን ለሚጠጋ ሕዝብ ለሶስት ወር የሚሆኑ ከ58 ሜትሪክ ቶን በላይ መድኃኒቶች እና በሌሎች ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በኩል ደግሞ 76 ሜትሪክ ቶን የሕክምና ቁሳቁስ መቅረቡ ተመልክቷል።

በተጨማሪም በመቀሌ የሚገኘው አይደር ሆስፒታል ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የጤና ሚኒስቴር ማደንዘዣን ጨምሮ የተለያዩ መድኃኒቶችን በዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበር እና በዓለም ጤና ድርጅት በኩል ለማድረስ እየተዘጋጀ መሆኑን አስታውቋል።



# ኢትዮጵያ ከዓለም ባንክ የ210 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ አገኘች

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ባንክ ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የከርሰ ምድር ውሃን ለማልማትና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የ210 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ አገኘች።

ድጋፉ የዝናብ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የከርሰ ምድር ውሃን በማልማት ለመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን እንዲሁም ለመስኖ ልማት ለማዋል ለተቀረጹ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ነው ተብሏል።

ፕሮጀክቶቹ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና በመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር በ5 ዓመታት ውስጥ የሚተገበሩ ሲሆን፣በቆላማ አካባቢ የሚኖሩ የሀገሪቱን ወገኖች ተጠቃሚ እንደሚያደርጉ ተገልጿል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አመራሮችና ባለሙያዎች ከዓለም ባንክ ልዑክ ጋር የተወያዩ ሲሆን፥ የድጋፍ ስምምነቱ በገንዘብ ሚኒስቴር ከተፈረመና በሀገሪቱ ፓርላማ ከፀደቀ በኋላ ተግባራዊ ይሆናል ነው የተባለው።

ፕሮጀክቶቹ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ውስጥ የከርሰ ምድር ውሃ በብዛት በሚገኝባቸው፣ ዝናብ አጠርና ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች አካል መሆናቸውን ከውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

# በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ምሩቃን የሚቀርቡ ሥራ ፈጠራዎችን ማበረታታት እንደሚገባ ተገለጸ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ምሩቃኖች ለገበያ እየቀረቡ ያሉ ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን ማበረታታት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከንቲባዋ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ያዘጋጀው 12ኛው ‹‹የቴክኒክ ሙያና ቴክኖሎጂ ሣምንት›› መክፈቻ መርሐ ግብር ላይ እንደገለጹት፤ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ችግር ፈቺ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና ጥራት ለገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። ጥረታቸው ግቡን እንዲመታ ኅብረተሰቡ ለአገራዊ ምርቶች ያለው አመለካከት ተስተካክሎ ምርቶችን መግዛትና መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል።

የሚታሰበውን ሀገራዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና የሚያፈልቁትን ሀሳብ ወደ ተግባር በመቀየር ውጤት ማስመዝገብን ይጠይቃል ያሉት ከንቲባዋ፤ ሀሳብ አፍላቂዎች ሀሳባቸው ወደ ተግባር ተቀይሮ የሕዝባችንን ችግር እንዲፈቱ በሁሉም መስክ ያሉ ባለሙያዎችን መደገፍና መበረታታት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ባለሙያዎችና ማዕከሎቻችን የከተማዋን ችግሮች መፍታት መጀመራቸውን አስታውሰው፤ በተለይም በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እጥረት እየቀረበ ያለውን እሮሮ መፍቻ ቁልፍ መንገድ ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው። በመሆኑም ከማንኛውም ሥራችን


ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

አስቀድመን ለእነዚህ ባለሙያዎች ድጋፍ በመስጠትና በማበረታታት የበለጠ ሥራ እንዲሠሩ ለመደገፍ እንሠራለን ብለዋል።

ከቴክኖሎጂ አንጻርም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ማነቆ ለመፍታት ለሕዝቡ የገባነውን ቃል ለመፈጸም የሚያስችል ድጋፍ ከቴክኒክ ሙያ ተቋማት ሙያተኞች እያገኘን ነው ያሉት ወይዘሮ አዳነች፤ የእነዚህ ተቋማት መልካም ሥራ ብቻውን የሚፈለገውን ውጤት ስለማያመጣ ኅብረተሰቡ ለአገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ ሰጥቶ ገዝቶ በመጠቀም፣ በየደረጃው ያሉ አመራሮችም አስፈላጊ ግብዓቶችን በማቅረብና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ውጤታማ ሥራ እንዲሠሩ ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር በከር ሻሌ በበኩላቸው፤ የችግሮችን ማሸነፊያ አቅምና ክህሎት ማደግ የሀገራችን የመፍጠርና የማድረግ አቅም ይገነባል። ክህሎትን በማሳደግና ብቁ ሙያተኞችን በማፍራት የሀገሪቱን ቁሳዊና ሰብዓዊ ጸጋ በመጠቀም ለችግሮቻችን መፍትሔ ለመስጠት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል።

የችግር ቁልፍ መፍትሔ ልገሳ ሳይሆን ክህሎትና ችሎታ መፍጠር ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የአገራችን የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች በዋናነት ማተኮር የሚገባቸው ችግሮችን ወደ እድል ለመቀየር የሚያስችል አቅም በመፍጠር የዜጎችን የመሥራት ፍላጎትና እውቀት ማሳደግ ላይ መሆን አለበት ብለዋል።

የልማታችንና የብልጽግናችን ማዕከል ሰው ነው ያሉት ዶክተር በከር ሻሌ፤ የሀገራችንን የልማት ፍላጎት የሚያሳኩ ብቁ ዜጎችን ለመፍጠር የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ማዕከላት መተኪያ የላቸውም። በመሆኑም ለዘርፉ የሚሰጠውን የተሳሳተ አመለካከት በመቅረፍ ተቋማቱ ችግር ፈቺ ብቁ ዜጎችን እንዲያፈሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ለእነዚህ ተቋማትና ሙያተኞች አስፈላጊው ድጋፍ እንደሚያደርግ ሚኒስትር ዴኤታው ጨምረው ገልጸዋል።

12ኛው የቴክኒክ ሙያና ቴክኖሎጂ ሳምንት "ሙያና ቴክኖሎጂ ለምርታማነት" በሚል መሪ ቃል የሚካሄድ ሲሆን ከግንቦት 30 እስከ ሰኔ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ እንደሚቆይ ታውቋል።


ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

ዶክተር ደረጄ ዱጉማ

# በኢትዮጵያ የወባ በሽታ 16 በመቶ ጨመረ

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የወባ በሽታ በ16 በመቶ መጨመሩንና በአስር ወራት ብቻ 1ነጥብ 3ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው መያዛቸውን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ በትላንትናው እለት ከኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን በወባ ወረርሽኝ፣ በኮሮና ቫይረስና እና የዝንጀሮ ፈንጣጣ ዙሪያ መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የጤና ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ደረጄ ዱጉማ እንደገለፁት፤ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የወባ በሽታ በ16 በመቶ መጨመሩንና በአስር ወራት ብቻ 1ነጥብ 3ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው ተይዘዋል።

ዶክተር ደረጄ እንዳብራሩት ፤ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወባን ለመከላከል 300 ሚሊዮን ብር በላይ መድቦ ለክልሎች አከፋፍሏል። ወረርሽኙን ለመግታትም ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ ነው።

ዶክተር ደረጄ በገለጻቸው፤ መሥሪያ ቤታቸው በየሳምንቱ ከየክልሉ መረጃ እየወሰደ በፍጥነት ምላሽ የመስጠት ሥራን እየከወነ ይገኛልም ብለዋል።

የወባ ታማሚዎች ቁጥር እየተበራከተ መምጣቱን ያመላከቱት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ በአስር ወራት ብቻ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሰዎች በወባ በሽታ መያዛቸውን አስታውቀው፤ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር፣ በሀገሪቱ የወባ በሽታ በ16 በመቶ ጨምሯል ብለዋል።

በአፍሪካ ውስጥ ከ75 በመቶ በላዩ አካባቢ ለወባ ወረርሽኝ ምቹ መሆኑን ያመላከቱት ዶክተር ደረጄ፤ በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2021 ብቻ 14 ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው የተያዙ ሲሆን 90 በመቶው ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት መሆኑንም አመልክተዋል።

ባለፉት አራት ወራትም በተለይ በደቡብ ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ወረርሽኙ መጨመሩን ተናግረዋል። አጎበር በአግባቡ አለመጠቀም፣ የአመራሩና ኅብረተሰቡ መዘናጋት፣ ለወረርሽኙ መስፋፋት በምክንያትነት ጠቅሰዋል።

እንደ ዶክተር ደረጄ ገለፃ፤ ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ መፈጠሩ እንዲሁም የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የወባ መድሀኒት ርጭት ያለመካሄዱ የታማሚዎችን ቁጥር ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል።

በተጨማሪም ዶክተር ደረጄ ድርቁን ተከትሎ የተከሰተው ከባድ ዝናብ ለወባ ወረርሽኝ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ተናግረዋል፡ ፡

በሌላም በኩል ባሳለፍነው ሳምንት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ዳግም መስፋፋቱንና 14 ሰዎች በፅኑ ህሙማን ክፍል እንደሚገኙ አመላክተው ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባውም አሳስበዋል።

በተጨማሪም ከሰሞኑ አነጋጋሪ እየሆነ የመጣው የዝንጀሮ ፈንጣጣ እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ አልተገኘም ነገር ግን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፤ በሽታው ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባም በ20 የድንበር ኬላዎች ላይ ቁጥጥር በመደረግ ላይ መሆኑም ጠቁመዋል ።

# ‹‹ከነዳጅ ጋር ተያይዞ ኢኮኖሚው ላይ ጫና እንዳይፈጠር በዲፕሎማሲና የሰላም ጉዳዮች ላይ መሥራት ይገባል››

ረዳት ፕሮፌሰር ዘገዬ ጳውሎስ
-የኢኮኖሚ ምሑር

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡ መንግሥት ከነዳጅ ድጎማ ውስጥ ቀስ በቀስ ከመውጣት ጋር ተያይዞ ኢኮኖሚው ላይ ጫና እንዳያሳድር በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲውና በሰላም ጉዳዮች ላይ መሠራት እንዳለበት ተጠቆመ።

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ተባባሪ ዲን ረዳት ፕሮፌሰር ዘገዬ ጳውሎስ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት መንግሥት የነዳጅ ድጎማ ከማድረግ ቀስ በቀስ በሚወጣበት ወቅት የሸማቹ ማኅበረሰብ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

መንግሥት በነዳጅ ዋጋ ላይ ድጎማ በሚያደርግበት ወቅት የሸቀጥና ቁሳቁስ ዋጋ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ሊቀርብ እንደሚችልና ሸማቹ የመግዛት አቅም ሊኖረው እንደሚችል ተናግረዋል።

በአንፃሩ ነዳጅ ላይ የሚደረገው ድጎማ በሚነሳበት ወቅት የእቃዎች ዋጋ በዚያው ልክ ሊጨምር እንደሚችልና ሸማቹ ከዚህ በፊት ከሚገበየው ዋጋ በጨመረ መልኩ እንዲሸምት የሚያደርግ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሀገር ደረጃ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሁኔታ በሚኖርበት ወቅት እንዲህ አይነቶቹ ውሳኔዎች ሊመከሩ እንደሚችሉ የተናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር ዘገዬ፣ በተለያየ አቅጣጫ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጫና ላይ በሆነበት በዚህ ወቅት መሆኑ ዜጎች በቀጣይ ለተጨማሪ የዋጋ መናር ችግር ያጋልጣል ብለዋል።

ይህም የነዳጅ ድጎማው ተነስቶ የሸቀጥና የምርት ግብዓት ትራንስፖርት ዋጋ እንዲኖር መንስኤ እንደሚሆንና ባለሀብቶች ምርቶቻቸውን አምርተው



በሚሸጡበት ወቅት ይህን የትራንስፖርት ዋጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሸማቹ ከዚህ በፊት ከሚገዛበት ዋጋ በላይ ጨምሮ እንዲገዙ ያስገድዳል ብለዋል።

በተያያዘ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ በሚቀንስበት ወቅት የአምራቹን ዘርፍ ሠራተኛ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ በመገደብ በቂ ምርት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ ተጨማሪ ተፅዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ተናግረዋል።

ከዚህና በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች መንግሥት የሚያደርገውን የነዳጅ ድጎማ መቀነስ ጋር ተያይዞ በቀጣይ የሸቀጦች ዋጋ መጨመር የሚጠበቅ መሆኑን ምሑሩ ተናግረዋል።

በመሆኑም መንግሥት ማኅበረሰቡ ለከፋ የዋጋ መናር ችግር እንዳይጋለጥ ዋና ዋና የሚባሉ እርምጃዎችን በመውሰድ የዋጋ ጭማሪውን መግታት እንዳለበት የተናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር ዘገዬ ጳውሎስ፣ በቂ ምርት በማምረት መሠረታዊ የሸቀጦች ዋጋ እንዳይንር በማድረግ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪዎች የሚገኙበትን እድል በመፍጠር ነዳጅ የመግዛት አቅምን ማጎልበት እንዳለበት ጠቁመዋል።

በተለይም ሀገሪቱ በተለያዩ ምክንያቶች የዶላር እጥረት እየገጠማት በመሆኑ ይህን ችግር በዘላቂነት ሊፈቱ የሚችሉ እርምጃዎችን ከወዲሁ በመውሰድ የዶላር እጥረቱ እንዳይባባስ በትኩረት መሥራት እንዳለባት አንስተዋል።

ለዚህም የዲፕሎማሲ ሥራዎች በተጠናከረ መንገድ በመሥራትና ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በመሳብ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር የሚመጣበትን መንገድ በሰፊው መሥራት ዋነኛ ተግባር መሆን እንዳለበት አንስተዋል።

በሌላ በኩል የሀገር ሰላም ወደ ነበረበት የሚመለስና ሀገር ውስጥ የተረጋጋ ሰላም የሚኖር ከሆነ አምራቹ ዘርፍ በተረጋጋ መልኩ ምርቶችን በሰፊው በማምረት የምርት እጥረት እንዳይከሰት በማድረግ የራሱን ጉልህ ሚና ከመጫወቱም በላይ የሀገር መረጋጋት የውጭ ባለሀብቶች የመሳብ እድል በመኖሩ በኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ወደ ሀገር እንዲገቡ እድል ይፈጠራል ብለዋል።

የጦርነት አማራጮችን ሁሉ በማቆም አምራቹ ኃይል ተረጋግቶ ምርቶችን በማምረት ወደ ገበያ የሚያቀርብበትን መደላድል መፍጠር የመንግሥትና የማኅበረሰቡ ዋነኛ ሚና በመሆኑ ከድጎማው ጋር ተያይዞ ሊመጡ የሚችሉ ጫናዎችን መቋቋም እንደሚቻል ተናግረዋል።

# የሕወሓት የሽብር ቡድንን ሴራ በተገኘው ዓለም አቀፍ መድረክ ማጋለጥ ይገባል ተባለ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የሕወሓትን የሽብር ቡድን ሴራ ኢትዮጵያ ባገኘችው የዓለም አቀፍ መድረክ ሁሉ ማጋለጥ አለባት ሲሉ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አቶ ሱራፌል ጌታሁን አስታወቁ።

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አቶ ሱራፌል ጌታሁን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕወሓት ስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ በተለያዩ የአለም አቀፍ ተቋማት ላይ ተቀጥረው የገቡ ደጋፊዎች አሉት።አሁን ላይ ሕወሓትን በውሸት በመደገፍ በዲፕሎማሲው መስክ ጫና ሲያሳድሩ ቆይተዋል። በተቃራኒው መንግሥት ይህን እኩይ ሥራውን ለዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ማኅበረሰብ ማስረዳትና ግልጽ ማድረግ አለበት ብለዋል።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ የሕወሓትን ሴራ በተገኘው የዓለም አቀፍ መድረክ ሁሉ ለአፍሪካ ኅብረት ጭምር ማሳወቅና ኢትዮጵያ ለሰላም ቁርጠኛ መሆኗን ማረጋገጥ ይገባል። የሕወሓት ቡድን የሚያደርጋቸውን



አቶ ሱራፌል ጌታሁን

አስከፊ ተግባራት ሁሉ በተገኘው ዓለም አቀፍ መድረክ በማጋለጥ የኢትዮጵያን አቋምና እውነታውን ማሳወቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሱራፌል ማብራሪያ፤ አምባሳደር ሁነው የተሾሙ ሰዎች ቀዳሚ ሥራቸው በዓለም አቀፍ መድረክ የሕወሓትን ሴራ ማጋለጥ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ የጸጥታው ምክር ቤትን አባል ሀገራቱን የመጥራት መብቷን ተጠቅማ መጥራትና ስላለው እውነታ ማሳወቅ አለባት። የሕወሓት የሽብር ቡድን አሁን ቢሆን ጦርነት ለማካሄድ እየፎከረ መሆኑን፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ደግሞ ለሰላም ቁርጠኛ መሆኑን ማስረዳት ይገባል። ምዕራባውያን የፈለጉትን ያክል የሚዲያ አውታር ቢይዙም ኢትዮጵያ እውነት ስለያዘች ማስረዳት ከቻለች ታሸንፋለች ብለዋል።

አሸባሪው ቡድን እስረኞችን ለቅቄያለው በማለት የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብን እያወናበደ ነው ያሉት አቶ ሱራፌል፤ በሌላ በኩል በአፋር ክልልና በወልቃይት በኩል ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ ደግሞ በአንድም ይሁን በሌላ ምዕራባውያኑ የሚያውቁትና በዘመዶቻቸው አማካኝነት ሕወሓት ለሰላም ቁርጠኛ እንደሆነ አድርገው በማሳየት የማደናገሪያ ስልታቸው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ስለዚህም የሽብር ቡድኑን እንቅስቃሴ በአግባቡ ለተቀረው ዓለም በአግባቡ ማስረዳት ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

## የመከላከያ ሠራዊቱ ቦንፍ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የነበረን የሸኔን ማሰልጠኛ አወደመ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ከሚያዝያ 17 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ሠራዊቱ ሌት ተቀን ባከናወናቸው ተግባራት መተከል ዞን ድባጤ ወረዳ ቦንፍ የሚገኘውን የሸኔ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ያወደመ ሲሆን 43ቱ ላይ እርምጃ ተወስዶ 60 የሸኔ አባላት ደግሞ በሰላም እጅ ሰጥተዋል።

በዚህም አሸባሪው ሲጠቀምባቸው የነበሩ 184 ኋላቀር መሣሪያዎች፣ 23 ክላሽንኮቭ፣ ከ300 ኩንታል በላይ በቆሎ፣ 16 ኩንታል አኩሪ አተር፣ ሁለት የፀሐይ ኃይል ማመንጫ (ሶላር)፣ ሁለት የእህል ሚዛን እና ሁለት ማዳበሪያ አደንዛዥ ዕፅ መያዙን ከመከላከያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

አሸባሪው ከኅብረተሰቡ ዘርፏቸው የነበሩ 47 የቀንድ ከብቶችና 60 ፍየሎችንም ማስመለስ መቻሉን መረጃው አክሎ አብራርቷል።

ለ3 ዓመታት በድባጤና በቡለን ወረዳዎች በሸኔና ፅንፈኛ ታጣቂዎች ስር የነበሩ 4 ቀበሌዎችም ነፃ ወጥተዋል። በተገኘው አንፃራዊ ሰላም ተፈናቃዮችን ወደ አካባቢያቸው እየተመለሱ እና ማኅበራዊ አገልግሎቱን በማስጀመር ላይ መሆናቸውን የተናገሩት ደግሞ የድባጤ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሙሉዓለም ዋወያ ናቸው።

ዋና አስተዳዳሪው አቶ ሙሉዓለም 273 ታጣቂዎች በኮማንድ ፖስት ስልጠና ተሰጥቷቸው አካባቢያቸውን በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።



## በቤኒሻንጉል ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መንግሥት የሰላም አማራጭ በመከተል ባደረገላቸው የሰላም ጥሪ እስካሁን በዳንጉር፣በማንዱራና በከፊል ድባጤ ወረዳዎች የሚንቀሳቀሱ 1ሺህ 700 ታጣቂዎች ወደ ሰላም ሲመለሱ በቡለን ወረዳም የመመለስ ፍላጎት ማሳየታቸውን አመልክተዋል።

የትጥቅ ትግል በመምረጥ እስካሁን ምላሽ ያልሰጡ በተለይ በወንበራና በጉባ ወረዳዎች መንግሥት ሕግ የማስከበር ኃላፊነቱን ለመወጣት ጠንካራ ቅንጅታዊ ኦፕሬሽን እያካሄደ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፣ አሁንም ቢሆን የጉሙዝ ሕዝብ ጥያቄም ሆነ የየትኛው ብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ ምድር በዴሞክራሲያዊ አግባብ እንጂ በኃይል እንደማይመለስ በመገንዘብ በወሬ ተታልለው ጫካ የገቡ ወጣቶች በሰላም መንገድ እንዲመለሱ ጠይቀዋል።

በሰላማዊ መንገድ ለተመለሱ ወጣቶች ተሐድሶ በመስጠት በፍላጎታቸው መሠረት ወደ የተለያዩ የሙያ ዘርፍ ለማሰማራት ርብርብ እየተደረገ መሆኑንም አቶ አብዮት አስታውቀዋል።

## ዋጋ ማስተካከያው በነዳጅ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ ከጎረቤት ሀገራት የችርቻሮ ዋጋ ከእጥፍ በላይ ልዩነት አለው፤ ኬንያ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያና ሱዳን ነዳጅ የሚሸጠው በኢትዮጵያ ከሚሸጥበት ከእጥፍ ዋጋ በላይ በመሆኑ የኢትዮጵያን ነዳጅ መጠቀም ጀምረዋል ብለዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ነዳጅ ወደ ጎረቤት ሀገራት እየወጣ ነው። ሀገር ውስጥም ለጥቁር ገበያ በር ከፍቷል። ኢትዮጵያ ከምትፈልገው ተጨማሪ የነዳጅ ፍጆታ ፍላጎት ፈጥሯል፤ አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ነዳጅ የሚሸጠው በርካሽ ዋጋ ከመሆኑ የተነሳ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪና የነዳጅ ብክነት ማስከተሉንም አመልክተዋል።

በነዳጅ ላይ እየተስተዋለ ያለውን ሕገ ወጥነት ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል። በሐምሌ ወር የሚደረገው የታለመለት የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ ከጎረቤት አገራት ጋር ተቀራራቢ እንዲሆን በማድረግ የኮንትሮባንድ ንግድ ለማስቆም ኢጋዥ ይሆናል ነው አቶ ለሜሳ ያሉት።

አንዳንዱ ማደያ ላይ ነዳጅ መድረስ አለመድረሱን በአካባቢው ንግድ ጽሕፈት ቤት ተረጋግጦ መረጃ እንዲሰጥና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቷል። መመሪያው ተሽከርካሪዎች ለየትኛው ከተማና ማደያ እንደ ጫኑ የሚረጋገጫ መልዕክት መለዋወጫ ተበጅቶለታል። ነዳጅ በበርሜልና በጀሪካን የሚሸጥበት ሁኔታ መልክ እንዳይዝ እንደሚደረግም አመልክተዋል።

ዋጋው ሲስተካከል በጎረቤት ሀገራት መካከል ያለው ልዩነት ኮንትሮባንድን የማይጋብዝ ከሆነ የኮንትሮባንድ ንግድ ይቀራል። ክትትል፣ የመረጃ ልውውጥና በጥቁር ገበያው የሚከናወነውን ሽያጭ መቅረፍ እንደሚያስችልም ገልጸዋል።

በነዳጅ ግብይት ዙሪያ በርካታ ችግሮች የሚስተዋሉበት ነው። የዋጋ፣ የነዳጅ መሠረተ ልማትና ሎጂስቲክስ፣ ትራንስፖርት፣ የማደያዎች እጥረት፣ ከአሠራር፣ ከትትልና ቁጥጥር ጋር ተያይዞ የሚመጡ መሠረታዊ ችግሮች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

የነዳጅ ግብይቱን በዋናነት ችግር ውስጥ እየከተተ ያለው እየተሸጠ ካለበት ዋጋ ጋር የተያያዘ ነው ያሉት አቶ ለሜሳ፣ የነዳጅ ዋጋ የሚወሰነው በዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ ተመን ሳይሆን በመንግሥት ነው። ነዳጅ የሚገዛው በዓለም የነዳጅ ዋጋ ሲሆን፤ የሚሸጠው መንግሥት በሚወስነው ዋጋ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ዋጋን የሚረጋጊያ ሥርዓት እንጂ የነዳጅ የድጎማ ፖሊሲ፣ አሠራርና የሕግ ማዕቀፍ ስለሌላት በነዳጅ ላይ ያለውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር በዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ ውስጥ ያለው እዳ 132 ቢሊዮን ብር መድረሱን አቶ ለሜሳ አስታውሰዋል።

ይህም የሆነው አንድ ሊትር ነዳጅ ጅቡቲ የሚደርሰው በ66 ብር ሲሆን ወደ አገር ውስጥ ሲገባ አንድ ሊትር ላይ ሰባት ብር ወጭ ተደርጎበት 73 ብር ጨርሶ የሚደርስ ቢሆንም እየተሸጠ ያለው ከመጣበት ዋጋ በእጥፍ ቀንሶ ነው። የእዳ ልዩነቱ 36 ብር በላይ የደረሰ ሲሆን የሚደጎመውም ይህ ነው። ነገር ግን የሚከፈል ዕዳ እንጂ ድጎማ አለመሆኑን አቶ ለሜሳ ገልጸዋል።

## የ2015 ረቂቅ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዓመት ጋር ሲነጻጸር ቅናሽ እንዳለው የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት ለዕዳ ክፍያ፣ ለመከላከያ፣ ለመልሶ ማቋቋም፣ ለእለት ዕርዳታ እንዲሁም ለማዳበሪያና ስንዴ ድጎማ የተመደበው በጀት ድርሻ 37 ነጥብ ሶስት በመቶ ሆኖ በመጨመሩና መሆኑን አስታውቀዋል።

ለአብነትም ለዕዳ ክፍያና ለመከላከያ ብቻ የተመደበው የወጪ በጀት ከአጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት መደበኛና ካፒታል ወጪ ውስጥ ያለው ድርሻ 37 ነጥብ ሶስት በመቶ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለዕዳ ክፍያ ፣ ለመከላከያ፣ ለዕለት ዕርዳታና ለማዳበሪያ ድጎማ የተደለደለው በጀት 239 ቢሊዮን ብር መሆኑን ገልጸዋል።

ከጠቅላላ የወጪ በጀት ውስጥ ደግሞ ለመደበኛ ወጪ 345 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ፣ ለካፒታል ወጪ 218 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ተመድቧል። በተጨማሪ ለክልል መንግሥታት ድጋፍ 209 ነጥብ አራት ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 14 ቢሊዮን ብር መቅረቡን አቶ አሕመድ አስረድተዋል።

የ2015 ጠቅላላ የፌዴራል መንግሥት ገቢ የውጭ ዕርዳታን ጨምሮ 477 ነጥብ 8 ቢሊዮን እንደሚሆን መታቀዱን ጠቁመው፣ ከዚህ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ምንጭ የሚሰበሰበው ገቢ 92 በመቶው የሚሆነውን ድርሻ መያዙን ገልጸዋል።

ከአገር ውስጥ ገቢው 400 ቢሊዮኑ ከታክስ ለመሰብሰብ ታቅዷል ያሉት አቶ አሕመድ፣ ዕቅዱ ከፍተኛ በመሆኑ ውጥኑን ለማሳካት የታሰቡትን የታክስ ፖሊሲና አስተዳደራዊ ማሻሻያዎችን በፍጥነትና በውጤታማነት ሥራ ላይ ማዋል ይጠይቃል ብለዋል።

በተጨማሪ ታክስ ካልሆኑ ምንጮች 38 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል። ይህም በ2014 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ ከታቀደው አንጻር የ10 በመቶ ብልጫ አለው። ገቢውንም ከብሔራዊ ባንክና ከንግድ ባንክ እንዲሁም ከሌሎች ተቋሟት ከሚገኘው ትርፍ፣ ከባለበጀት ተቋማት አገልግሎት ክፍያዎች፣ ከመንግሥት ዕቃዎች ሽያጭና ከተለያዩ ገቢዎች የሚሰበሰብ መሆኑን ተናግረዋል።

በ2015 በጀት ዓመትም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከነበራት በማገገም ዘጠኝ ነጥብ ሁለት በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ መተንበዩን አቶ አሕመድ ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በሌላ በኩል የ2015 ረቂቅ በጀት ላይ የ231 ነጥብ አራት ቢሊዮን የተጣራ የበጀት ጉድለት እንደሚያጋጥም ተገምቷል። ጉድለቱን ለመሸፈን 224 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ከሀገር ውስጥ ብድር እንዲሁም ስድስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብሩን ደግሞ ከውጭ የተጣራ ብድር ይወሰዳል።

የረቂቅ በጀቱ የበጀት ጉድለቱ ከዚህ ቀደም ከነበረው ጊዜ ሲነፃፀር ከፍ ያለ መሆኑን ያነሱት አቶ አሕመድ፤ የዋጋ ንረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል ብለዋል።

የዋጋ ንረትን በተመለከተም በ2014 ዓ.ም ሚያዚያ ወር ላይ 36 ነጥብ 6 በመቶ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አሕመድ፤ ግሽበቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ነጠላ አኃዝ ማውረድ እንደሚከብድ ጠቁመዋል።

በ2015 በጀት ዓመት አስፈላጊ የፖሊሲና መዋቅራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ የዋጋ ግሽበቱን ወደ 11 ነጥብ 9 በመቶ ለማውረድ መታቀዱን አስረድተዋል።

በአጠቃላይም የተዘጋጀው ረቂቅ በጀት ከአምናው ጋር ሲነፃፀር ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት አንፃር ግን በቂ አለመሆኑን ሚኒስትሩ አንስተው፤ ፈፃሚ አካላት ቁጠባን መሠረት በማድረግ ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

ፈፃሚ አካላት የመንግሥትን የግዢ ሥርዓት አክብረው እንዲሠሩና ወጪ ቆጣቢ አሠራሮችን መከተል እንደሚገባቸው ገልጸዋል።

የበጀት አፈጻጸም ላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቁጥጥሩን አጥብቆ እንደሚቀጥል ገልጸው፤በቁጥጥርና ክትትል ውስጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ለሚኒስቴሩ ድጋፍ እንዲያደርግም ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሺዴ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ዲያስፖራ ከአሸባሪ ድርጅት ደጋፊነት ወጥቶ የትግራይ ሕዝብ ድምጽ ሊሆን ይገባል!

በአንድ ማኅበረሰብ ላይ የተደቀነን አስከፊ ችግር ለመፍታት ከሁሉም በላይ የዚያ ማኅበረሰብ አባላት በቀዳሚነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። የችግሩን ምንጭ ከማወቅ አንስቶ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል መነቃቃት፤ ለዚህም የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠርም ይኖርባቸዋል።

ችግሮችን ከራስ ጥቅምና መሻት ውጪ ማየት የሚያስችል የተከፈተ ዓይን ፤ ሕዝብን ተራ የፖለቲካ መሸቀጫ ካርድ አድርጎ ከመጠቀም ክፉ እርግማን መውጣትንና ራስንና የራስ የሆነውን ነገር ሁሉ ማኅበረሰቡን በእውነትና በእውነት ብቻ ለመታደግ በሚያስችል የልብና የሕሊና ንጽሕና ውስጥ ማስገዛት የሚጠይቅ ትልቅ ማኅበራዊ ከዛም በላይ ሰብዓዊ ኃላፊነት ጭምር ነው።

ከወቅታዊ የፖለቲካ ስካር ፤ስካሩ ከሚፈጥረው እብደት ወጥቶ ችግሮችን በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ማየትን ፤ የዛሬው እብደት በነገው ትውልድ እጣ ፈንታ ላይ ሆነ እንደ ማኅበረሰብ በማኅበረሰቡ ነገዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋና ማኅበራዊ ጽልመት ኃላፊነት በሚሰማው መልኩ ማጤንንም የሚጠይቅ ነው።

ከዚህ አንጻር የትግራይ ሕዝብ እንደ አንድ ማኅበረሰብ ላለፉት 50 ዓመታት በአሸባሪው ሕወሓት እየደረሰበት ስላለው ችግር ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ከእሱ አብራክ ወጥተው በተለያዩ የዓለም ክፍላት የሚገኙ የዲያስፖራ አባላት ለቀባሪ ማርዳት ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም።

ቡድኑ ገና ከውልደቱ ጀምሮ ከተጠናወተው የጥፋት ተልዕኮ ፤ ስለ ነጻነት፣ ፍትሕና ዲሞክራሲ ከፍ ባለ ድምፅ ያዜም በነበረው ዜማ ታምነው የበረሀውን ትግል የተቀላቀሉ የትግራይ ወጣቶችን ሳይቀር በነበራቸው የሀሳብ ልዩነት ለእልቂት የዳረገ ፤በክልሉ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ሌሎች የትግራይ ኃይሎችን አጥፍቶ በመቃብራቸው ላይ ራሱን ያቆመ በክፋትና በሴራ የተካነ ቡድን ነው ።

ስለ ነጻነትና ዲሞክራሲ እያዜመ የትግራይን ሕዝብ ምንም አይነት አማራጭ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዳይኖረው በቀደመው ዘመን በአንድ ለአምስት አሁን አሁን ደግሞ አንድ ለሶስትና አንድ ለሰላሳ በመጠርነፍ በማኅበረሰብ ውስጥ የአስተሳሰብ ብዝኃነት እንዳይሰፍን አድርጓል፤ እያደረገም ነው ። ሕዝቡን በማስጨነቅ ተስፋ ቢስ አድርጎ በተስፋ መቁረጥ መንፈስ የእድሜው ማስረዘሚያ አቅም አድርጎታል ።

የትግራይ ሕዝብ እንደ አንድ በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንደሚኖር ፤ ከዚያም በላይ በቀደመው ዘመን ከፍያለ የስልጣኔ ታሪክ ባለቤት እንደሆነ ትልቅ ሕዝብ ሳይሆን የራሱ ፈቃድና ፍላጎት እንደሌለው፤ ስለ ራሱ ማሰብና መወሰን እንደማይችል ሕዝብ ከፍ ባለና በማያፈናፍን የአፈና መዋቅር ራሱንና የራሱን መሻት እንዳይኖር አድርጎታል ።

የቡድኑ የዕድሜ መግዣ የመስዋዕት በግ ከማድረግ አልፎ በሃይማኖተኛነቱ ፤ በቅንነቱ እና ፈጣሪን በማክበር የሚታወቀውን የትግራይን ሕዝብ ከቀደመ ማንነቱ ጋር እንዲጣላ ፤ በማንነት ቀውስ ውስጥ እንዲወድቅና የትውልዶች ዝቅጠት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ለዘመናት በፍቅር በመከባበርና በመቻቻል ከኖራቸው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር እንዲጋጭ እየሄደበት ያለበት የሴራ መንገድ በትግራውያን ስነ ልቦና ላይ እየፈጠረ ያለው ግርዶሽ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ቡድኑ በስልጣን በቆየባቸው 27 ዓመታት በትግራይ ሕዝብ ስም የሀገርን ሀብት በታቀደና በተደራጀ መንገድ ከመዝረፍ ባለፈ ለትግራይ ሕዝብ ያመጣለት አንዳች ፋይዳ የለም ።የትግራይ ሕዝብ በነጻነት ትግል ስም ልጆቹን ከመገበር ባለፈ ከቡድኑ ያገኘው ትሩፋትም ፈጽሞ የለም ። ቀደም ባለው ዘመን የኖረው በእርዳታ ነው፤ በኋለኛውም ዘመን እስከ ዛሬ እየኖረ ያለው በእርዳታ/በሴፍቲ ኔት/ ነው።

በቀደመው ዘመን የትግራይ ወጣቶች በነጻነት ስም በተደረገ የትጥቅ ትግል በትግራይ የፖለቲካ መድረክ የአንድ ቤተሰብ መንግሥት/ ኢምፓየር ከመገንባት ያለፈ ለትግራይ ሕዝብ ያመጡለት አዲስ ነገር የለም ።በ21ኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ መሳፍንት መንፈስ የታጀሉ መንደርተኞችን በደማቸው ሕይወት ሰጥተው በራሳቸው ላይ አንግሰዋል። ይህ የቀደመው ትውልድ ትልቁ አሳዛኝ ታሪክ /ትራጀዲ /ነው ።

ከዚህ ታሪካዊ እውነታ ሶስተኛው የሕወሓት ትውልድ፤ ዲያስፖራውና መላው የትግራይ ሕዝብ ሊማር የሚገባቸው ተጨባጭ ትምህርት ስለመኖሩ አነጋጋሪ አይደለም። አሸባሪው ሕወሓት ከውልደቱ ጀምሮ የትግራይን ሕዝብ የነጻነት፤ የዲሞክራሲና የልማት ጥያቄ ጥያቄው አድርጎ እንደማያውቅ፤ ከዚህ ይልቅ ሁሌም የትግራይን ሕዝብ አግቶ ለሕልውናው ዋስትና የማድረግ ቁመራ ላይ የሚገኝ ፤ ለዚህም ምንም አይነት የሞራል እንጥፍጣፊ የሌለው ተፈጥሯዊ ሞቱን የሞተ ድርጅት ነው።

ከዚህም በላይ ዛሬ ላይ ዓይኑን በጨው ታጥቦ የትግራይ ሕዝብ የነገ ተስፋ የሆነውን ወጣቱን ትውልድ በተለመደው የገለማ የነጻነት ዲስኩር ለእልቂት በመዳረግ ለተፈጥሯዊ ሞቱ ትንሳኤ ለመፍጠር ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ በሆነ የጥፋት መንገድ ላይ ይገኛል።ይህ መንገድ የትግራይን ሕዝብ ሊያስከፍለው ከሚችለው ከፍ ያለ ዋጋ አንጻር የትግራይ ሕዝብም ሆነ ዲያስፖራው ከቡድኑ የቀደመ ታሪክ ተነስተው በቃህ ሊሉት ይገባል ።

በተለይም ከቡድኑ አፈና መዋቅር ውጪ ያለው የዲያስፖራው ማኅበረሰብ ካለበት የፖለቲካ ውዝግብ ወጥቶ በትግራይ ቀደም ባለው ዘመንም ሆነ አሁን እየሆነ ያለውን ነገር በሰከነ መንፈስ በማጤን የትግራይ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በቡድኑ የተጋረጠበትን አደጋ ለመታደግ ሊነሳ ለዚህ የሚሆን መነቃቃት ሊፈጥር ይገባል። ለትግራይ ሕዝብ ድምጽ ሆኖም ሊጮህ ይገባል። ይህን ሳያደርግ በመቅረቱ ለሚከሰተው ችግር የሚኖረው ተወቃሽነትና የጥፋተኝነት መንፈስ የከፋ እንደሚሆን ለማሰብ አይከብድም!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የትግራይ ሕዝብ ልጆቹን ከአሰቃቂ እልቂት ለመታደግ አሸባሪውን ሕወሓት በቃህ ሊለው ይገባል !

ሰላማዊት ውቤ

አሸባሪው ሕ.ወ.ሓ.ት ወደ ትጥቅ ትግል ከገባ 50 ዓመታትን እያስቆጠረ ነው ። ቡድኑ የብሄር አጀንዳን ይዘው ጫካ የገቡት መሪዎቹ 27 ዓመታት ኢትዮጵያን የማስተዳደር ዕድል ቢያገኙም ዛሬም ድረስ የትግራይን ሕዝብ እርዳታ ጠባቂነት ፍፁም ሊያድኑት አልቻሉም።

በስልጣን በቆዩባቸው 27 ዓመትም ለትግራይ ህዝብ የፈየዱለት ነገር የለም። የትግራይ ሕዝብ ከ1966ቱ ዓ.ም ድርቅ ባልተለየ ሁኔታ ዛሬም በብድኑ እብሪት የተነሳ ብዙ ዋጋ እየከፈለ ነው ። በ27ቱ ዓመታት የስልጣን ዘመኑ ተጠቃሚ የሆኑት የስርአቱ ጥቂት አሽቃባጮች እና የአንድ ቤተሰብ አባላት ናቸው ።

ቡድኑ የማይጨበጥ የቅዠት ነጻነት አጎናጽፋችኋለሁ ብሎ ጦርነት ከጀመረ ሦስተኛ ትውልድ እየመጣ ቢሆንም፤ መሪዎቹ በየጊዜው በሚፈጥሯቸው ችግሮች ምክንያት ትውልዶቹ የቡድኑ መቆመሪያ ከመሆን ያለፈ የተሻለ እጣ ፈንታ አላጋጠማቸውም ።

ለትግራይ ህዝብ እንደገቡለት ቃልም ትግራይን የጦርነት አውድማ እንጂ ምድረ ገነት ማድረግ አልሆነላቸውም። ጭራሽ ዓይጥ እንዳየች ድመት ልጆቹን እያሳደዱ ለማያባራ ጦርነት በመማገድ ስጋት ሆነው ሲያባንኑት ኖሩ እንጂ። ያሉትን ነፃነትም አሁን ድረስ አላጎናፀፉትም ።

‹‹የበሉበትን ወጪት ሰባሪ›› ሆነው ከትግራይ ሕዝብ አልፈው የኢትዮጵያን ሕዝብን ጭምር ለከፋ ችግር ዳርገዋል እሁንም እየዳረጉ ነው። በህዝባዊ አመጽ ከስልጣን ከወረዱ በኋላም የትግራይን ህዝብ መሸሸጊያ በማድረግ ለስልጣናቸው የመቆመሪያ ካርድ አድርገውታል።

ዘንድሮ ህፃን ልጅ እንኳን በቤት እቤት ጨዋታ በማያደርገው በዚህ ሥራቸው ከመረረው የትግራይ ሕዝብ ጋር ተፋጥጠዋል። በነፃነት ስም ምድሩ የጦርነት አውድማ፤ ልጆቹ ጭዳ እየሆኑ ከትውልድ ትውልድ ዕድሜ ብቻ ሲቆጥር መኖሩ ሰልችቶታል። አንዳች ጠብ የሚል ነገር በሌለበት፤ ልጆቹንና ገንዘቡን እነሱ በየጊዜው ለሚያስነሱት ጦርነት ሲገብር መቆየቱም በእጅጉ አስቆጭቶታል።

**ከትግራይ ሕዝብ ጋር የተፋጠጠው ሕ.ወ.ሓ.ት ዘንድሮ ቅጣ አንባሩ ጠፍቶታል። ከትግራይ ሕዝብ ጋር በመፋጠጡ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቷል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢሆን ዛሬ ወደ 1966ቱ ዓ.ም ተመልሶ በረሃብና በቸነፈር የገረጣና የተጎዳ የትግራይ እናቶችን ፊት በፍፁም ማየት አይሻም**

የእርዳታ እህል ይግባ አይግባ በሚል እንዲሁም በገዛ ነፃነቱ ጉዳይ ጭቅጭቅ አስልችቶታል። ደግሞም አስቆጥቶታልም! ‹‹ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል›› እንዲሉ መሪዎቹ ያን ያህል ዓመታት ወስደው ያልጠቀሙት ዛሬ ይጠቅሙኛል የሚል ዕምነቱ ተሟጧል።

መሪ ነን ለሚሉትና በስሙ ሲነግዱ በቆዩት ሕ.ወ.ሓ.ቶች ጠብ በማይል ቁም ነገር ጆሮውን መስጠት አልዋጥ ብሎታል። በማይጨበጥ የቅዠት ዓላማ አወጫብረው በስልጣን እርከን ላይ ለመፈናጠጥና ስልጣንን እርስትና ጉልታቸው አድርገው ለመቆየት የሚያደርጉት እንደሆነ አውቋል።

በዚህ ሁኔታ ከትግራ ሕዝብ ጋር የተፋጠጠው ሕ.ወ.ሓ.ት ዘንድሮ ቅጣ አንባሩ ጠፍቶታል። ከትግራይ ሕዝብ ጋር በመፋጠጡ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቷል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢሆን ዛሬ ወደ 1966ቱ ዓ.ም ተመልሶ በረሃብና በቸነፈር የገረጣና የተጎዳ የትግራይ እናቶችን ፊት በፍፁም ማየት አይሻም።

በተለይ የትግራይ ተጎራባች ክልሎች የሆኑት አማራና አፋር ሕ.ወ.ሓ.ት በማያባራ ጦረኝነቱ የትግራይን ሕዝብ መከተቱ ፤ ወጣቱን የጦስ ዶሮ ማድረጉ እነሱም በየጊዜው መተንኮሳቸው ሰልችቷቸዋል።

የአማራ ክልላዊ መንግስት በዚህ ወር ያወጣው መግለጫም ይሄንኑ ነው የሚያመለክተው ። በዚሁ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ፖቲከኞችም አስተያየት ሰጥተዋል። መንግስትም የአማራውን መግለጫ በመደገፍ መግለጫ አውጥቷል። ሁሉም መንግስታት በዚሁ ጉዳይ ላይ ምክክር እንዳደረጉና በተጠንቀቅ ላይ እንደሆኑም የገለጡበት ሁኔታ ተስተውሏል።

የትግራይ ሕዝብ ይሄን ሁሉ የመታዘብ ጊዜ አግኝቷል። አመራሮቹ አሁንም በጥፋት መስመር ላይ እንደተሰለፉ እንደሆኑም በሚገባ እያስተዋለ ይገኛል። ቢቢሲ እንደዘገበው ልጆቻቸውን የመጨረሻ ላለው የማያባራ ጦርነት ካልገበሩ ከ20 እስከ 40 ሺህ ብር የደረሰ የቅጣት ገንዘብ እንዲከፍሉ የማስፈራሪያ ማዕቀብ መጣሉም የትግራይን ሕዝብ በእጅጉ አስቆጥቶታል።

ይሄን ማስፈራሪያ የምዕራቦቹ ሚዲያዎችም በማራገብ የሕ.ወ.ሓ.ት አመራሮችን ሲወቅሱበት ሰንብተዋል። አሁን ላይ የሱዳንን በር በማስከፈት ፤ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ሕ.ወ.ሓ.ት (ወያኔ) ትግራይ ላይ ቁጭ ብሎ አማራና አፋርን ጨምሮ በክልል መንግስታት ዙሯዬን ተከብቤያለሁ ፤ እርዳታ መግባት ፤ አልቻለም እያለ የሚደነፋው ከሕዝቡ ጋር በመፋጠጡ መሆኑም እንኳን ለክልሎች ለሕዝቡም አልጠፋው።

በዚሁ ወር በአፋር በኩል በተከፈተው የእርዳታ ማስገቢያ ኮሪደር 64 እርዳታ የጫነ መኪና ወደ ትግራይ መግባቱን እርዳታዎች ወደ ክልሉ እየገቡ እንደሆነ ትግራይ ህዝብ ቀርቶ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ውሎ አድሯል።

በተጨማሪም በዚሁ ሰሞን የአለም ባንክ ትግራይን ጨምሮ በጦርነቱ ከአማራና አፋር ክልሎች ለተፈናቀሉ ዜጎች ድጋፍ የሚውል 300 ሚሊዮን ዶላር እርዳታ መስጠቱን የዚሁ እውነታ ማሳያ ነው።

የሕ.ወ.ሓ.ት አመራሮች (ሌቦችና ወንጀለኞቹ) ግን ዛሬም የመጨረሻ በሚሉት የአጥፍቶ መጥፋት ጦርነት ለመግባት እየተዘጋጁ ነው ፤የትግራይንም ወጣት ለከፋ እልቂት ለመዳረግ ሌት ተቀን እየተጉ ነው ። ይህንን እውነታ ለመቀልበስ የትግራይ ህዝብ ግንባር ቀደም ሊሆን ይገባል። ልጆቹን ከቀጣይ እልቂት ለመታደግ ቡድኑን በቃህ ሊለው ይገባል!

# ፍረዱኝ

## በመጦሪያ እድሜዬ ልጆቼ ጎዳና ሊጥሉኝ ነው!

(እማሆይ አለምነሽ ወንድም አገኘሁ)

ሙሉቀን ታደገ

የዛሬው የፍረዱኝ አምድ ዝግጅታችን በመዲናችን በአዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ ስድስት በተለምዶ ጎፋ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በአንድ ቤተሰብ መካከል የተፈጠረ ውዝግብን ይዳስሳል። በደል ተፈጽሞብናል ሲሉ ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቤት ያሉት የ86 ዓመት አዛውንት የሆኑት እማሆይ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ልጃቸው ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ናቸው።

የ86 ዓመት አዛውንቷ እማሆይ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ፣ በንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ ስድስት በ834 የቤት ቁጥር ነዋሪ ናቸው። በዚህ ቤት አምስት ልጆችን እና በርካታ የልጅ ልጆችን በማሳድግ ለወግ ለማዕረግ እንዳበቁበት አዛውንቷ ይናገራሉ።

ይሁን እንጂ በአሁን ወቅት ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ የተባለችው ልጃቸው እና ልጆቿ (የልጅ ልጆቻቸው) ልጆቻቸውን እና የልጅ ልጆቻቸውን ካሳደጉበት ቤት ሊያስወጧቸው እንደሆነ ይናገራሉ። በእርጅና ዘመናቸው እጦርበታለሁ፤ እቀበርበታለሁ ካሉት ቤት ፍትህን እና ሞራልን ባልተከተለ አኳኋን ሊያባርሯቸው መሆኑን ያስረዳሉ።

«በዚህ እድሜዬ ለጎዳና ከመዳረጌ በፊትም የኢትዮጵያ መንግስት እና ህዝብ የተፈጸመብኝን አሳዛኝ ድርጊት በመመልከት ይፍረደኝ!» ሲሉ ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል። የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ እና ቀኙን በማየት መፍረድ ይችል ዘንድ ዝግጅት ክፍሉ የደረሰበትንሙሉ የምርመራ ውጤት እነሆ ብሏል። መልካም ንባብ።

### ውዝግብ የፈጠረው ቤት የኋላ ታሪክ

የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ከዛሬዋ አቤቱታ አቅራቢ እማሆይ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ ጋር ሁለት ጉልቻ የመሰረቱት በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ነበር። ጥንዶቹ በትዳር ዘመናቸው በቀለች ሃይሌ ፣መድሃኒት ሃይሌ ፣ ፍቃዱ ሃይሌ ፣አየለች ሃይሌ እና ሰለሞን ሃይሌ የተባሉ አምስት ልጆችን ወልደው ለመሳም ቻሉ። የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ወታደር በመሆናቸው ከባለቤታቸው ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ከአምስት ልወጆቻቸው ጋር በካምፕ ውስጥ መኖር የውዴታ ግዴታ ነበር። ስለሆነም ከልጆቻው ጋር ለበርካታ ዓመታት በካምፕ አሳልፈዋል።

የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ከአጼ ሐይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት የመጀመሪያ አምስት አመታት ድረስ እናት ሀገራቸውን በውትድርና አገልግለዋል። በንጉሱ ዘመን በሰሩት ወታደራዊ ጀብዱም በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት እንዲሰጣቸው በመንግስት ይወሰናል። በዚህም አሁን ላይ ጎፋ መብራት ሃይል ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ባዶ ቦታ ተሰጣቸው። ጎፋ ሰፈር አሁን ያለበት ደረጃ እጅግ ጥሩ ቢባልም የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሲሰጣቸው ግን አካባቢው ጫካ እና ያልለማ ነበር። የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ቤት ሰርተው ቤተሰባቸውን በራሳቸው ቤት ለመኖር ከነበራቸው ጉጉት ያልለማውን ጫካ መንጥረው ለቤት መስሪያ አዘጋጁት። ነገር ግን በስንት ውጣ ውረድ ጫካ መንጥረው ያለሙትን ቦታ ለመብራት ሀይል ልማት ሊውል በመታሰቡ ቦታውን ለመንግስት እንዲለቁ ተደረገ።

ይህ በእንዲህ እያለ ጎፋ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ቀደም ብሎ ሌተናል ኮሎኔል በቀለ ባልቻ በተባሉ የጦር መኮንን በርስትነት ሲተዳደር የሚኖር አንድ ቦታ ነበር። ኮሎኔሉ በርስትነት ሲያተዳድሩት የነበረውን ቦታ በመተው ሌላ ቦታ ላይ ቤት ይሰራሉ። ይህን ተከትሎ ለመብራት ሃይል ልማት በሚል ጫካ መንጥረው ያለሙትን ቦታ የተነጠቁት የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ፣ ሌተናል ኮሎኔል በቀለ ባልቻ በርስትነት ይዘውት የነበረው ቦታ ይሰጠኝ ሲሉ በ1966 ዓ.ም ለጽህፈት ሚኒስቴር ያመለክታሉ። ጉዳዩም በጽህፈት ሚኒስቴር ተቀባይነት አግኝቶ በሰኔ ወር 1966 ዓ.ም በቁጥር 3661/8/116/01 ለአዲስ አባባ ከተማ ማዘጋጃ የተባለው ቦታ እንዲሰጣቸው ማዘዣ ደብዳቤ ተላከ። የአዲስ አባባ ከተማ ማዘጋጃም 116/3ዕ/67 በቀን 7/2/1967 ዓ.ም



ለርስት እና መሬት ቅየሳ ዋና ክፍል ደብዳቤ ተጻፈ። በደብዳቤውም ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ የጠየቁት ጥያቄ ተቀባይነት ስላገኘ እንዲፈጸምላቸው የሚያዝዝ ነው። በዚህም መሰረት ኮሎኔሉ በይዞታነት ሲያስተዳድሩት የነበረው አምስት መቶ ካሬ ሜትር ለሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ በ1967 ዓ.ም ተሰጡ።

የአምስት ልጆች አባት የሆኑት ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ፣ በ1971 ዓ.ም ለግዳጅ በምስራቅ ኢትዮጵያ ግዛት ስር በምትገኘው ገዋኔ እየተባለች ወደ ምትጠራው አካባቢ ለግዳጅ ተላኩ። በዚሁ ዓመት ሻለቃ ባሻ ሀይሌ በግዳጅ ላይ እያሉ አምስት ልጆቻቸውን ተመልሰው ላያዩ ይችን ምድር ተሰናበቱ።

የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤተሰቦች የካምፕ ህይወትም በዚሁ አመት አበቃ። ወይዘሮ አለምነሽ እና ልጆቻቸው የካምፕ ህይወትን በመተው ዛሬ ላይ ውዝግብ በተነሳበት ቦታ አመሩ። ይህን ተከትሎ የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ባለቤት የሆኑት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ የልጆቻቸው ሞግዚት መሆናቸውን በ1972 ዓ.ም በህግ አሳወጁ። ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ልጆቻቸው ህይትን ያለሻለቃ ባሻ ሃይሌ ሊያስቀጥሉ ግድ ሆነ።

በወቅቱ ለሀገራቸው ሲሉ መሰዋዕት የሆኑ የወታደር ልጆች በውጭ ሀገር በመሄድ እንዲማሩ መንግስት እድሉን ያመቻች ስለነበር ወይዘሮ መድሃኒት እና አቶ በፍቃዱ ሃይሌ የተባሉት የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ልጆች በ1972 ዓ.ም ለትምህርት ወደ ሀገረ ኩባ ተላኩ።

ወደ ሀገረ ኩባ የተላኩት የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ልጆች አቶ በፍዱ ሃይሌ እና ወይዘሮ ማህሌት ሃይሌ በቤተሰብ ናፍቆት ሳቢያ በተፈጠረ መጨናነቅ ለከፍተኛ ድብርት እና ህመም ተዳረጉ ። በሀገረ ኩባ በባይታወርነት እየተሰቃዩ መኖር እንዲያበቃ በመወሰን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የሚመለከተውን አካል ጠየቁ። በዚህም አቶ በፍዱ ሃይሌ በ1977 ዓ.ም ወደ እናት ሀገራቸው ሲመለሱ ፤ ወይዘሮ ማህሌት ሃይሌ ደግሞ ወንድማቸውን ተከትለው 1978 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ።

ሁለት ልጆቻቸውን ወደ ሀገረ ኩባ የላኩት እናት ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ፣ ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከተባሉት ልጆቻቸው ጋር አብረው ይኖሩ ነበር ። በቤተሰቡ ውስጥ የነበረው ፍቅር ለሰፈር የሚያስቀና ነበር ።ከውርስ ጋር ተያይዞ አንዳቸው አንዳቸውን መጠራጠር ብሎ ነገር አልነበረም። ወደ ኩባ የሄዱት ልጆች ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ያረፉትም በእናታቸው እና በአባታቸው ቤት ነበር።

ቀንን ቀን ሲወልደው ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ የተባሉት የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ እናታቸውን ወይዘሮ አለምነሽን በምስጢር ቤቱን እንዲያወርሷቸው ይጠይቃሉ። ወይዘሮ አለምነሽም ለማንም ጉዳዩን ሳያሳውቁ እና ሳይሰሙ በ1985 ዓ.ም ቤቱን ለወይዘሮ በቀለች ብቻ ያወርሳሉ።

ነገሩን በምስጢር ማድረጋቸው እየቆየ የከነከናቸው እናት ለልጃቸው ያወረሱትን ቤት ከልጃቸው መውሰድ ፈለጉ። ቤቱን እንድትመልሳልቸውም ልጃቸውን ይጠይቃሉ። ልጅም ቤቱ የእኔ እንጂ ያንቺ ስላልሆነ ቤቱን እንድመልስልሽ የመጠየቅ መብት የለሽም ይላሉ።

ይህን ተከትሎ አራቱ ልጆች ስለጉዳዩ ሳያውቁ እና ሳይሰሙ እናት ወይዘሮ አለምነሽ በ2000 ዓ.ም በውርስ የሰጠኋትን ቤት ትመልስልኝ ሲሉ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱት። ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቶ እናት በፍርድ ቤት ክርክር ይረታሉ። እናትን የፍርድ ባለዕዳ እንዲሆኑ ያደረጋቸውም ቤቱን ለልጃቸው ካወረሱት በርካታ አመታት በመቆጠሩ የይርጋ ጊዜ ገደብ አልፎበታል በሚል ነበር።

እውነት እና እሳትን አፍኖ ማቆየት ይቻል እንደሆን እንጂ እስከመጨረሻው መደበቅ አይቻልም እንዲሉ በ2006 ዓ.ም የሻለቃ ባሻ ቡሊ አራቱም ልጆች ስለጉዳዩ ይሰማሉ። የሰሙትን ማመን የከበዳቸው የሻለቃ ባሻ ልጆች እንዴት እንደዚህ ይሆናል? ሲሉ እናታቸውን እና እህታቸውን ይጠይቃሉ። እናት ሳያውቁ ተታልለው ለወይዘሮ በቀለች እንዳወረሱ እና ጉዳዩን በደንብ ከተረዱ በኋላ ግን በስጦታ ያወረሱትን ቤት ለማስመለስ እስከፍርድ ቤት መሄዳቸውን ለልጆቻቸው ያስረዳሉ።

ይሁን እንጂ በብቸኝነት ቤቱን የወረሰችው ልጅ ደግሞ ቤቱ የእርሷ እንደሆነ እና ስለቤቱ ማንም እንደማያገባው አስረግጠው ለወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ይነግሯቸዋል። ይህን ተከትሎ በፍቅር እና በመተሳሰብ አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ ብሎ ሲኖር የነበረው ቤተሰብ በመካከሉ ክፉኛ ነፋስ ገባው። ቤሰተቡ በከፍተኛ ደረጃ መግባባት ራቀው።

ይህ በእንዲህ እያለ እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኝ በ1971 ዓ.ም ባለቤታቸው በግዳጅ ላይ መሰዋታቸውን ተከትሎ በ1972 ዓ.ም ቤተሰቡን ለማሳድግ የሞግዚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከህጋዊ አካል የተቀበሉ ቢሆንም በቤቱ ላይ ህጋዊ ወራሽነታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመኖሩ ቤቱን ከባለቤታቸው በውርስ ስለማግኘታቸው የሚያረጋግጥ የባለመብትነት የምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ሲሉ በ2006 ዓ.ም ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አመለከቱ። ክፍለ ከተማውም ህጋዊ ወራሽ ስለመሆናቸው ቤቱንም በውርስ ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ እንደወረሱት የሚገለጽ ምስክር ወረቀት በ2006 ዓ.ም ይሰጣቸዋል።

ይህ በእንዲህ እያለ ቤቱ የአባታችን ስለሆነ ለእኛም ይገባናል ሲሉ የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ልጅ የሆኑት ወይዘሮ መድሃኒት፣ አቶ ሰለሞን፣ ወይዘሮ አየለች እና አቶ በፍቃዱ ለፍርድ ቤት አቤት አሉ።

### በፍርድ ቤት የነበረው ክርክር እና ውሳኔ

ከባለውርስ ባለመብትነት ጋር ተያይዞ በፍርድ ቤት የነበረው ክርክር ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ሰበር የደረሰ ሲሆን፣ ከስምንት አመት በላይ የፈጅቷል። ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው የፍርድ ቤት ክርክር ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ፣ አቶ ፍቃዱ ሃይሌ፣ ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከሳሽ፤ እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ወራሽ እህት በቀለች ሃይሌ በቀደም ተከተል አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል። በፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ከሳሽ ቤቱ የአባታችን ስለሆነ እና እኛም አንደኛ ደረጃ ህጋዊ ወራሽ ስለነሆን ከቤት ውርስ ጋር ተያይዞ የሚከናዎኑ ማናቸውም አይነት ተጠያቂሚ የሚያደርጉ መብቶች እኛንም ይመለከተናል አሉ። እናትም የመጀመሪያ ልጄ የወሆነችው ወይዘሮ በቀለች እኔ ያልተማርኩ በመሆኔ እኔን በማታለል ቤቱን ከልጆች ደብቃ ነው የወረሰችው። በመሆኑም ቀሪ ልጆቼም በቤቱ የሚኖራቸው መብት ይከበርላቸው ሲሉ ከሳሽ ልጆቻቸውን ደግፈው ቆሙ።

ሁለተኛ ተከሳሽ የሆኑት ወይዘሮ በቀለች በበኩላቸው፤ አራቱም ልጆች በወራሽነት ያልተመዘገቡ ስለሆኑ እና ከጅምሩ ቤቱ የእኔ እንጂ የእናታችንም ሆነ የአባታችን የሻላቃ ባሻ ሃይሌ ቤት ስላልሆነ ከሳሽ ወንድም እና እህቶቼ ከውርስ ጋር ተያይዞ ያነሱት የይገባኛል ጥያቄ አግባብነት የለውም ሲሉ ተከራከሩ።

ቤቱን የወረሱት ልጅ ከመጀመሪያም ጀምሮ ቤቱ የእኔ እንጂ በውርስ የተገኘ አይደለም ማለታቸውን ተከትሎ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ቤቱ የማን ነው? የሚለውን ለማጣራት ጉዳዩን ለውርስ አጣሪ አካል መራው። ይህን ተከትሎ የውርስ አጣሪው አካል ቤቱ በ1967 ዓ.ም ለሻለቃ ባሻ እንደተሰጣቸው እና በ1971 ዓ.ም ሻለቃ ባሻ በግዳጅ ላይ እያሉ በማረፋቸው በ1972 ዓ.ም እናት ወይዘሮ አለምነሽ ደግሞ ቤቱን የልጆች ሞግዚት ሆነው እንዳስተዳደሩት እንዲሁም በ1985 ዓ.ም ወይዘሮ አለምነሽ ለተከሳሽ ወይዘሮ በቀለች በስጦታ ውል ማስተላለፋቸውን ገልጾ ፤ ይሁን እንጂ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1195(1) መሰረት ከቤቱ ጋር ተያይዞ የምስክር ወረቀት ያገኘ ሰው በማይንቀሳቀስ ንብረት ሆኖ እንደሚቆጠርለት ስለሚደነግግ ቤቱን በስጦታ ውል እናት ስላስተላለፉት እና ቤቱን በመተመለከተ ወይዘሮ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

በቀለች የምስክር ወረቀት በህግ ከተፈቀደለት አካል ስለተሰጣቸው ከ1985 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ ወይዘሮ በቀለች የሚያስተዳደሩት የግል ንብረት እንጂ የውርስ ንብረት አይደለም ሲል መለሰ።

ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ባደረገው ተጨማሪ ምርምራ የውርስ አጣሪው የደረሰበት ውሳኔ ትክክል አይደለም በሚል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔ ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸና ሆነ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሁሉም ልጆች የወራሽነት ማረጋገጫ ከፍርድ ቤት እንዲያመጡ ተጠቀ። አራቱም ከሳሽ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾ መሆናቸው ተረጋገጠ ። ይሁን እንጂ ከሻለቃ ባሻ ሞት በኋላ ወደ ኩባ ያልሄዱት ልጆች የወራሽነታቸው መብታቸው በይርጋ ታገደ።

የይገባኛል ክርክሩም ኩባ በሄዱት ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከሳሽ እናት ወይዘሮ አለምነሽ እና ወራሽ ልጃቸው ወይዘሮ በቀለች ተከሳሽ ሆነው ቀረቡ። ክርክሩም እስከሰበር ሰሚ ችሎት ዘለቀ።

በክርክሩም ቤቱን በስጦታ ያወረስኩት ያልተማርኩ ስለሆነ በማታለል እና በማጭበርበር ነው ሲሉ እናት ለሁሉም ለፍርድ ቤቶች አስረዱ። ይሁን እንጂ የቤቱን ግማሽ ወይዘሮ በቀለች በስጦታ መውረሳቸውን እና አሁን ላይ ደግሞ የእናት ቤቱን የማስመለስ ህጋዊ መብት በይርጋ የተገደበ መሆኑን አስገንዘቦ በውርስ ለወይዘሮ በቀለች የተሰጠው ግማሽ ቦታ ለወይዘሮ በቀለች እንዲሰጥ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ወሰነ። ግማሹ የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ድርሻ ደግሞ ለሶስት ማለትም ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ፣ አቶ ሰለሞን ሃይሌ እና ለወይዘሮ በቀለች እንዲከፋፈሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ወሰነ።

በዚህ ውሳኔ መሰረት የቤቱ ግማሽ እናት ለወይዘሮ በቀለች በስጦታ ውል ያወረሱት ስለሆነ በወይዘሮ በቀለች ወራሽነት እንዲጸና እና ግማሹ የአባት ድርሻ ደግሞ ለሶስት እንደተካፈሉት ተወሰነ።

ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ፣ አቶ ፍቃዱ ሃይሌ ፣ ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ቦታውን እናታችን ከአባታችን ያገኘችው እንጂ በራሷ ያፈራችው ስላልሆነ ለአንድ ልጇ ብቻ የማውረስ መብት የላትም። ቤቱ የአባታችን ስለሆነ እና አባታችን ሲሞት አሁን ለክርክር የቀረቡት ልጆች ለአቅመ አዳም እና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ስለነበር እናት ልጆችን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ቤቱን በሃላፊነት ተሰጣት እንጂ አልወረሰችም። ስለሆነም የራሷ ልላሆነ ንብረት ማውረስ አትችልም ሲሉ ተከራከሩ።

በመጨረሻም ክርክሩን ሲያዳምጥ የነበረው ፍርድ ቤት የአከራካሪው ቤት ግማሽ የሚሆነው እናት ለወይዘሮ በቀለች ያወረሱት ስለሆነ ለወይዘሮ በቀለች የተሰጠው ቦታ ባለበት አንዲጸና እና ግማሹ የአባታቸው ድርሻ ደግሞ ከእናታቸው ውርስ ያገኙትን ወይዘሮ በቀለችን ጨምሮ ለሶስት እንዲከፋፈሉ ተወሰነ።

**ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቤት እንዲሉ ያስቻሉ አስገዳጅ ምክንያቶች**

የፍርድ ባለእዳን ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌን እና እናታቸውን እማሆይ አለምነሽ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤት እንዲሉ ያስገደዳቸው አንደኛው አብይ ምክንያት ከውርስ የተገለሉት ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ በእናት እና በአባት አንድ በመሆናቸው አንደኛ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች መሆናቸው እየታወቀ ኩባ ሀገር ስላልሄዱ ብቻ ከአባታቸው ድርሻ የወራሽነታቸው መብታቸው በይርጋ መታገዱ ትክክል አይደለም። ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከአባታቸው የወራሽነት ባለመብትነታቸው ከወይዘሮ በቀለች ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ በይርጋ መታገድ ካለበት የወይዘሮ በቀለችም በይርጋ መታገድ ሲገባው ከላይ የተጠቀሱት የቤተሰቡ አባል የወራሽነት መብት ነፍጎ ለወይዘሮ በቀለች ብቻ በይርጋ የማይታገድበት መንገድ ፍትሃዊ አይደለም።

ሌላው የፍርድ በለዕዳ የሆኑትን ወይዘሮ ማህሌት እና እናታቸውን ወደ አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ለአቤቱታ ያበቃቸው ነገር እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ ባለቤታቸው ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሌ እንደሞቱ በአመቱ በህግ የተፈቀዳላቸው ለአቅመ አዳም እና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ልጆችን በሞግዚትነት እንዲንከባከቡ እንጂ ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤቱን እንዲወርሱ አይደለም። ወራሽ ስለመሆናቸው የሚያሳይ ሰነድ የለም ። ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤቱን በህጋዊ መንገድ መውረሳቸው የሚመለከተው አካል አረጋግጦ ምስክር የሰጣቸው በ2006 ዓ.ም ነው። ይሁን እንጂ ይህ ህጋዊ የውርስ ሰነድ በሌለበት እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድም አገኘሁ በ1985 ዓ.ም ለለልጃቸው ለወይዘሮ በቀለች ሃይሌ አውርሰዋል። ይህ ደግሞ በግልጽ የሚታይ የህግ ክፍተት ያለበት ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቱ ወይዘሮ በቀለች ከእናታችን በስጦታ ያገኘናቸውን ውርስ በይርጋ ለወይዘሮ በቀለች ማገዱ አግባብነት የለውም።

ሌላውና በሶስተኛ ደረጃ የፍርድ ባለእዳዋ ወይዘሮ ማህሌት እና እናታቸውን ወደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለአቤቱታ ያመጣቸው አብይ ጉዳይ ደግሞ ከፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ የተተገበረው የፍርድ የአፈጻጸም አካሄድ ነው። የቦታው ግማሽ ለሶስት እንዲከፍል ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እያለ ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ በዓይነት ከማካፈል ይልቅ ቤቱ ጨረታ በማውጣት እንድንካፈል ለማድረግ ሲጥር ይስተዋላል። ይህ ደግሞ እናታችንን በዚህ እድሜዋ ጎዳና ላይ የሚጥል ነው ።

ቦታው በጨረታ ይሸጥ ቢባል እንኳን የፍርድ አፈጻጸም ለጨረታ ያወጣው የቦታው ልኬት ትክክል አይደለም። ቦታው በካርታ 500 ካሬ ሜትር ይሁን እንጂ የክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር ባደረገው የማጣሪያ ልኬት መሰረት የቦታው ስፋት 680 ካሬ ሜትር ነው። ይሁን እንጂ ህግ አፈጻጸም ቦታው 500 ካሬ ሜትር እንደሆነ በማስመሰል ቦታውን በአይነት ከማካፈል ይልቅ በሃራጅ እንዲሸጥ ጨረታ አወጣበት። የፍርድ አፈጻጸም ቢሮ አካሄድ ትክክል ስላልሆነ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይልኝ ሲሉ ለፍርድ ቤት እንደገና አቤት ማለታቸውን ወይዘሮ መድሃኒት ይናገራሉ። ፍርድ ቤትም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለፍርድ አፋጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ መጻፉን ያስረዳሉ።

የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮም የፍርድ ቤት ትዛዝን ተቀብሎ እንደገና ጨረታ አወጣ። ይሁን እንጂ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ አጠቃላይ የቦታው ስፋት 680 ካሬ ሜትር ሆኖ ሳለ የተስተካከለ ከክፍለ ከተማ የተሰጠን የቦታ ልኬት 580 ካሬ ሜትር ነው በማለት የቦታው ግማሽ 290 ካሬ ሜትር ለወይዘሮ በቀለች በመስጠት፤ ግማሹን 290 ካሬ ሜትር ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ በማውጣት ሊሸጥብን ነው። ይህ ደግሞ እናታችንን ጎዳና ላይ የሚጥል ውሳኔ ነው ሲሉ የፍርድ ባለእዳዋ ይናገራሉ ።

እናታችን የነርቭ ችግር ያለባት ስለሆነች እና ከወይዘሮ በቀለች ውጭ ያሉ ልጆቿም ተከራይተን የምንኖር በመሆናችን በኪራይ ቤት ደግሞ የነርቭ ችግር ያለበትን እና ራሱን ችሎ የማይጻዳዳን ሰው ለማኖር አከራዮች ፍቃደኛ ስለማይሆኑ እናታችን ለጎዳና ልትዳረግብን ስለሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግስት ይድርስልን ሲሉ የፍርድ በለእዳዋ ይጮኃሉ።

**ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ ምላሽ**


ጉዳዩን በበላይነት ሲከታተሉት የቆዩት በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ የቴክኒክ ክፍል ባለሙያ አቶ እስማኤል ኢብራሂም ይባላሉ። የቴክኒክ ክፍል ባለሙያው የሰጡትን ምላሽ እነሆ፡-

እንደ አቶ እስማኤል ገለጻ፤ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ በፍርድ ቤት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን በክፍለ ከተማ ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በማመሳከር የፍርድ አፈጻጸም ስራዎች ይከናወናሉ።

በዚህም መሰረት የፍርድ አፈጻጸም ቢሮው ከፍርድ ባለእዳ ወይዘሮ መድሃኒት እና በፍርድ ባለመብት ወይዘሮ በቀለች ጋር ተያይዞ ተፈጠረ የተባሉ ችግሮችን እንዴት እንደተፈጠሩ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አብራርተዋል።

አንደኛው ወይዘሮ መድሃኒት ጥያቄ ቦታው በአይነት ያካፍሉን የሚል ነው። ይህን ለምን በዓይነት ለማካፈል አልተቻለም? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ይጠይቃል። በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ የቴክኒክ ክፍል ባለሙያ የሆኑት አቶ እስማኤል እንደሚሉት፤ በአዲስ አባባ መሬት አስተዳደር መመሪያ መሰረት አንድ ቦታ ራሱን ችሎ ሊለማ የሚችለው 150 ካሬ ሜትር እና ከዚያ በላይ ስፋት ሲኖር ብቻ ነው። እነወይዘሮ መድሃኒት ለሶስት ይካፈሉት ተባለው ቦታ 290 ካሬ ሜትር ነው። ይህ ደግሞ ለሶስት ሲካፈል በአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር መመሪያ መሰረት ራሱን ችሎ መልማት ስለማይችል በዓይነት ለማካፈል አይቻለም።

የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ የመጀመሪያ ምርጫው የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን በዓይነት ማካፈል ነው። ይህ አልሆን ሲል በስምምነት ቦታው ተሽጦ እንዲካፈሉት ይደረጋል። ይህ አልሆን ሲል ደግሞ በሃራጅ ጨረታ ይወጣበት እና ቦታው ተሽጦ ፍርድ ቤት በወሰነው መሰረት ለእያንዳንዳቸው የድርሻቸው



እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

የእነ ወይዘሮ መድሃኒትም በአንደኛው እና በሁለተኛው አማራጭ የፍርድ አፈጻጸሙን ማስኬሄድ ባለመቻሉ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮው ሶስተኛውን አማራጭ ለመምረጥ ተገዷል።

የፍርድ ባለእዳዋ ወይዘሮ መድሃኒት ቤቱ መሬት ላይ ያለው ልኬት 680 ካሬ ሜትር ሆኖ ሳለ በካርታ ላይ ያለውን 500 ካሬ ሜትር ነው በማለት 250 ካሬ ሜትር ብቻ እንድንወስድ እየተደረገ ነው። በዚህ ደግሞ ለጨታ የቀረበው ቦታ ርካሽ እንዲሆን ያደርግብናል ሲሉ ይጠይቃሉ። ስለዚህ ምን ይላሉ? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ዳይሬክቶሬት ቢሮውን ይጠይቃል።

እውነት ነው ለመጀመሪያ ጊዜ በፍርድ አፈጻጸም ጨረታ የወጣበት በ500 ካሬ ሜትር ስፋት ብቻ ነበር። ነገር ግን የፍርድ በለእዳዋ ከክፍለ ከተማ አስጽፈው ባመጡት ደብዳቤ ቦታው 580 ካሬ ሜትር እንደሚለካ ስለተረጋገጠ የመጀመሪያው 250 ካሬ ሜትር ላይ የወጣው ጨረታ ተሰርዞ ለሁለተኛ ጊዜ ተስተካክልሎ 290 ካሬ ሜትር በሚል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጨረታ ወጥቷል።

ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የፍርድ በለዳዋ የሚሉት ቦታው 680 ካሬ ሜትር ይለካል ነው። እዚህ ላይ የእናንተ ምላሽ ምንድን ነው? የፍርድ አፈጻጸም ስራችን የምናከናውነው ከክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር በሚገኙት መረጃዎች መሰረት ነው። የክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር ደግሞ የላከልን ደብዳቤ ቦታው በካርታ 500 ካሬ ሜትር እንደሆነ እና በመሬት ላይ ልኬቱ ደግሞ 580 ካሬ ሜትር መሆኑን ነው። ስለዚህ እኛ ክፍለ ከተማው ከላከልን መረጃ ውጭ እንዴት ልናካፍል እንችላለን? ሲሉ ይጠይቃሉ። ክፍለ ከተማው የቦታው ልኬት 680 ካሬ ሜትር ነው የሚል ከሆነ በእኛ በኩል ለማካፈል ችግር የለብንም።

**የፍርድ ባለመብት ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ ቤተሰቦች ምላሽ**

ብሩክ ግርማ ይባላሉ፤ የፍርድ ባለመብቷ የወይዘሮ በቀለች ሃይሌ ልጅ ናቸው። የፍርድ ባለእዳ የሆኑት ወይዘሮ መድሃኒት እና አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት እማሆይ አለምነሽ እንደሚሉት፤ የተፈረደው ፍርድ ቤቱን እንድንካፈል የሚያዝዝ ነው። በዚህም የፍርድ ባለመብቷ ወይዘሮ በቀለች እናታችንን እማሆይ አለምነሽን ጎዳና እንድትወጣ እያደረጉ ነው ይላሉ። እዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቶ ብሩክን ጠየቀ።

ክርክሩ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ እናታችን ወይዘሮ በቀለች ካደገችበት ቤት በፍርድ ባለእዳዋ ወይዘሮ መድሃኒት እና ወንድሞቿ በግፍ እንድትወጣ ተድርጓል። በዚህም እናታችን ወይዘሮ በቀለች ሃይሉ ክርክሩ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በኪራይ ቤት እየተቸገረች እንድትኖር ተፈርዶባት ቆይቷል። በመጨረሻም ክርክር ከተነሳበት ቤት የሚገባትን ድርሻ በፍርድ ቤት ተወስኖላታል። ይህ ማለት እናታችን ወይዘሮ በቀለች እናቷን ወይዘሮ አለምነሽን ጎዳና አውጥታ ትጥላለች ማለት አይደለም። እናታችን እንደማንኛውም ልጅ እናቷን የመርዳት ሃላፊነቷን አለባት ። የፍርድ ባለእዳዎች እንደሚሉት እናታችን እናቷን ጎዳና ላይ የምትጥል ሰው አይደለችም ። ምክንቱም ወይዘሮ በቀለች ሰባዊነት የተላበሰች ሰው ከመሆኗም ባለፈ እናቷን ወይዘሮ አለምነሽ መርዳት ሞራላዊ ግዴታዋ መሆኑን ጠንቅቃ ትገነዘባለች ሲሉ ይናገራሉ።

እንደሚታወቀው፤ የፍርድ ባለ እዳዎች ክርክር ከተነሳበት ቤት በወራሽነት ተጠቃሚ ናቸው። ስለሆነም እነርሱም እንደ ልጅ እናታችንን ሊረዱ ይገባል። እኛም እንደ ልጅ የሚደርስብንን ሃላፊነት እንወጣለን ሲሉ ይገልጻሉ።

በፍርድ ቤት የተወሰነው ውሳኔ ቦታው ይከፈል የሚል ነው። ነገር ግን ቦታው መከፈል ስለማይችል ጨረታ ወጥቶበታል። በጨረታ ከተሸጠ ደግሞ እማሆይ አለምነሽ መኖሪያ አያገኙም የሚል ስጋት በፍርድ ባለዳዎች በኩል ይነሳል። እማሆይ አለምነሽ በእድሜ የገፉ ከመሆናቸው አንጻር የሚቆዩት ጊዜ እምበዛም እንደማይሆን ይገመታል። ስለሆነም ከሞራል አንጻር እናታችሁን ለምን ፍርድ ቤት እንድትካፈሉት ባዘዘው ቦታ ቀሪ እድሜያቸውን እንዲያሳልፉ አታደርጉም? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የወይዘሮ በቀለችን ልጅ አቶ ብሩክን ጠየቀ።

አቶ ብሩክም እኛ የፍርድ ቤት ውሳኔን መሻር አንችልም። ቤቱ መከፈል አይችልም። ስለሆነም በጨረታ ተሽጦ መከፈል አለበት። ይሁን እንጂ እኛም እንደ ልጅ እናታችን ጎዳና እንዳትወጣ የበኩላችንን ለመርዳት ዝግጁ ነን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "አስለቃሾች አያስቅሱም፤"

**ዝክረ ሰሙነ ቀብር፤**

አበውና እመው፤ "አቤቱ ፈጣሪ ሆይ ሞቴንና አሟሟቴን አሳምርልኝ" የሚሉት የተለመደ የሠርክ ጸሎት አላቸው። ይህ የተማጽኖ ጸሎት ካዘቦት ቀናት መቃተት ከፍ ብሎ የብዙኃን ምኞት ወደ መሆን ደረጃም ያደገ ይመስላል። ምኞት ብቻም ሳይሆን "አሟሟቱ በክብር እንዲጠናቀቅ" ጭምር "የስዕለት ኪዳን የሚገባ" ዜጋም ይጠፋል ተብሎ አይታሰብም። ብዙኃን ዜጎች በዚህን መሰሉ "አሟሟቴን አሳምርልኝ" ምልጃ ከመማረካቸው የተነሳም ጉዳዩ በማኅበረሰባችን ውስጥ ሥር የሰደደ እምነት ወደ መሆን ደረጃ የተሸጋገር ሳይሆን እንደማይቀርም ይገመታል። ሞት በቀጠሮ ያለመምጣቱ እንጂ ነገሩ ባልከፋ ነበር።

በሀገራችን ብሔረሰቦች ዘንድ ሞትና የቀብር ሥነ ሥርዓት ልዩ ቦታና አትኩሮት እንደሚሰጠው ቢታወቅም ክዋኔው ግን ከቦታ ቦታ፣ ከአካባቢ አካባቢ እንደሚለያይ የታወቀ ነው። በአንዳንድ አካባቢ ለሟቹ የሚደረገው የሽኝት ባህልና የቀብር አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ለቀናት የሚሰነብት ሆኖ ዝግጅቱም በስፋት የሚተገበር ነው። የሟቹ ታሪክ ምንም ይሁን ምን ሙገሳና ክብር ግን አይጓደልበትም። በአንዳንድ አካባቢዎች አስከሬን የሚሸኘው በፉከራ፣ በቀረርቶና በጭብጨባ ጭምር ታጅቦ ነው። የፉከራውም ሆነ የቀረርቶው ይዘት ግን የግድ በሟቹ/ቿ ግለሰብ ላይ ብቻ ላያተኩር ይችላል። መገፋት፣ የፍትሕ እጦት፣ የበደል ቁጭት ያለበት ቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ ወይንም ጎረቤት የቀብሩን ሥርዓት ምክንያት አድርጎ ብሶቱን የሚገልጽባቸው በርካታ አጋጣሚዎች የተለመዱ ናቸው።

ይህ ርዕሰ ጉዳይ ብዙ ስለሚያጽፍ ለጊዜው ገደብ አበጅቶ በሙሾ ረገዳ ላይ ብቻ ለማተኮር ይሞከራል። ሙሾ፡- የለቅሶ ቅንቀና፣ ዥመራ፣ ግጥም፣ ዜማ፣ ቁዘማ፣ እንጉርጉሮ፣ ረገዳና ጭብጨባ የታከለበት በቀብር ወቅት የሚፈጸም ክዋኔ መሆኑን መዛግብተ ቃላቱ ይተነትናሉ። በተለይም በከተሞች አካባበቢ (ለገጠሩ ባህል ብዙም እውቀት ስለሌለኝ ነው) የዕለት እንጀራቸውን በሙሾ አውራጅነት ላይ የመሰረቱ በርካታ ሴትና ወንድ "ስልጡን ባለሙያዎች" መኖራቸው የታወቀ ነው።

እነዚህ ቀብር አድማቂ አስረጋጆች ውሏቸው ማስለቀስ እንጂ እነርሱ በነጋ በጠባ ገንዘብ ለከፈላቸው ሁሉ እንደማያለቅሱና የእምባ መዋጮ እንደማይለግሱ በሚገባ ይታወቃል። ይህ ጸሐፊ ባደገበት የምዕራቡ አዲስ አበባ ክፍል ዝናቸው የናኘ በርካታ አስለቃሾች እንደነበሩ ያስታውሳል። ከሦስት አሠርት ዓመታት በፊት የዚሁ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተወዳጅ እህት በነበረችው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ስለ ሙሾ አውራጆቹ ዝርዝር ጉዳዮች እንደጻፈም ያስታውሳል።

ዛሬ ዛሬ ልምምዱ የደበዘዘ ይምሰል እንጂ የሙሾ ድርደራና ደረት ማስደቃቱ ሙሉ ለሙሉ ቀርቷል ለማለት ያደግታል። የሟች የቅርብ ዘመዶች ከገደብ አልፈው ፊታቸውን እንዲነጩና በርካታ ጊዜያትም በገላቸው ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ሙሾ አሙሻዎቹ አስለቃሾች ምክንያት ይሆናሉ እየተባለ ቢወገዝና የሕግ ቁጥጥር እየተደረገበት ለቅጣት ሰበብ እስከመሆን ቢደረስም ክዋኔው ግን ዛሬም ድረስ ከባህሉ ውስጥ ተሟጦ ጠፍቷል ለማለት ያዳግታል።

የሙሾ ደርዳሪ አስረጋጆች ለአስለቃሽነት አገልግሎታቸው የሚከፈላቸው የገንዘብ መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ ሀዘንተኞቹ የሚያቀርቧቸው ሌሎች ማትጊያዎችም እንደሚሟሉ ማሕበረሰቡ በሚገባ ያውቀዋል። ለምሳሌ፡- ለአስለቃሽነት አገልግሎት የሚመረጠው ግለሰብ በቅድሚያ ማነቃቂያ እንዲሆን ጠጅ፣ ጠላም ሆነ አረቄ እንዲቀርብለት ይደረጋል። ከቀብር በፊትም ሆነ በኋላ (አስከሬኑ አፈር ቀመሰም አልቀመሰ) ተገቢው የምሳ አቅርቦት የተለመደ ነው። እናም በአስለቃሾች (ሴትም ሆነች ወንድ) የሚጠይቀው ዳረጎት በሚገባ ከተሟላ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር "ወደ ሥራ" ገብቶ ዋይ ዋይ እያሰኙና ለማስመሰል ያህል ደረትን ነካ ነካ እያደረጉ ለቀስተኛውን በእንባ ማራጨትና ፊት ማስነጨት ዋና ግቡ ነው። "አልቃሽ ያስለቅሳል እንጂ አያለቅስም" የሚባለውም ስለዚሁ ነው።

**ለቅሶ እያለ ከቤት፤ ማድላት ለጎረቤት፤**

በወቅታዊው የሀገሬ አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ መቆዘም ስጀምር ፈጠኖ የሚታወሰኝ "ሕዝብን ማስለቀስ እንጂ፤ ራሳቸው የማያለቅሱ" ብዙ አስረጋጆች እንደ አሸን የመፍላታቸው ጉዳይ አንዱና ጊዜ ወለዱ መከራችን ነው። እነዚህ አስለቃሾች የሕዝቡን ስሜት እየኮረኮሩ በማጫጫህ ደረት ለማስደቃት የተካኑ ናቸው። በእነርሱ ቤት "ሁሉም ሀገራዊ ጉዳይ ሞቶ ለቀብር ጊዜ የሚጠብቅ ነው።" ሞተ፣ ተቀበረ እያሉ በሚቀባዥሩባቸው ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ ዜጎች እምባ እንዲራጩና ተስፋ እንዲቆርጡ የማይጠቀሙበት ዘዴ አይኖርም። ራሳቸውን የሚጠሩትም አንድም አክቲቪስት አለያም ፖለቲከኛ ወይንም ጋዜጠኛ እያሉና እያሰኙ ነው።

የማሕበረሰቡ ለቅሶና ዋይታ ደስታ የሚፈጥርላቸው እነዚህን መሰል "ዘመናዊ አስለቃሾች" ዳረጎታቸውን የሚያገኙት ከተለያዩ የጎረቤትና የሩቅ ጠላቶች ዘንድ ነው። ለዴሞክራሲ ትንታኔ የፈጠኑ፣ ለትችት ምላሳቸውን ያሰሉ፣ ለበጎነት የተኮነኑና "ሁሌም ሀገር ሞታ እንድትቀበር" ለሰይጣን የሚካድሙ "ሙሾ አሙሻዎች" ሀገር ጤና ውሎ እንዲያድር በፍጹም ፍላጎት የላቸውም። ሕዝብም ተረጋግቶ ሲኖር ማየት ይቀነቅናቸዋል።

የእነርሱ ደስታ ሕዝብ በትንሽ በትልቁ ሲማረር መስማት ነው። ማስለቀሱን እንጂ አብሮ ማልቀሱ እርማቸው ስለሆነ ፉከራቸውና ቀረርቷቸው ሁሌም "ሀገር ፈጥና ትሙትና እንቅበራት" የሚል ይዘት ያለው ነው። ሀገሬ በስንቱ ደዌ እንደማቀቀች ትኖራለች!? ሕጉና ሥርዓቱም ጠበቅ ብሎ በአስለቃሾች ላይ አስተማሪ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እስከ መቼ እንዳሸለበ እንደሚኖር ሊገባን አልቻለም።

እነዚህ "የማሕበረሰብ አስለቃሾች" እንደ ሕዝቡ ርሃብ አያውቁ፣ ጥማት አይሞክራቸው፣ ሁሌም ጠግበው እንዳገሱ ነው። የአይዞህ ባዮቻቸው ዳረጎት ልባቸውን ስላሳበጠና የሚሰክሩበት "የፕሮፓጋንዳ ወይን ጠጅ" አናታቸው ላይ ወጥቶ ስላሰከራቸው፤ የፈለጉትን ተናግረውና ሰርተው ቢውሉ ሃይ ባይ ተቆጪ የሌለ እስኪመስል ድረስ ሲፋንኑ የሚባጁት በየአደባባዮች ላይ ነው።

ብዙዎቹ አስለቃሾች ኑሯቸውን የሚገፉት በሁለት ባላ ላይ ተንጠልጥለው ስለሆነ የኑሮ ጉድለትም ሆነ የገቢ ጠብሽ አያውቃቸውም። ብዙውን ጊዜ ሕዝቡን ወደ ተስፋ ማስቆረጥ የቀብር ስሜት ውስጥ ይከቱትና እነርሱ ግን በማግሥቱ በግራና በቀኝ በያዙት ፓስፖርት አንዱን መዘው ወደ ከፉ ቀን ማረፊያቸው እብስ ይላሉ። ነገር ሲቀዘቅዝም ቀድሞ አደባባይ በመታዬት ገና ከአውሮፕላን እንደወረዱ በሙሾ ግጥም እምባ ማራጨቱን ይጀምራሉ። እውነት እንነጋገር ከተባለ መንግሥትም ቢሆን እንደ በኩር ልጅ እሹሩሩ እያለ ለማባበል የሚፈጥነው እነዚህኑ አስለቃሾች እስኪመስል ድረስ ግራ ያጋባል።

ስለ እውነት እንመስክርና "የእጃችንን አሻራ በምድራችን ላይ በትነን" በሙያችን ለማገልገል የሀገርን ጥሪና የሕዝብን የድረሱልኝ አደራ አክብረን ከተመቻቹ ሀገራት ጓዛችንን ሸክፈን የመጣን በርካታ ዜጎች የአስለቃሾቹን ያህል ትኩረትም ሆነ ግምት የተሰጠን ስለመሆኑ ያጠራጥራል። "ከአልቃሾቹ ይልቅ የአስለቃሾችን እምባ እያበሰች" ሀገሬ እስከ መቼ እንደምትጓዝ መልሱ ርቆብን ግራ እንደተጋባን እነሆ ዕድሜያችንን እንደቆጠርን አለን።

በአግባቡ እውቂያ ያለን አንድ ወዳጄ በነጋ በጠባ ሙሾ እያሞሸ ሲማረርና ሌሎቹም እንዲማረሩ ሲያደርግ አስተውዬው ድርጊቱ አግባብ እንዳልሆነ ስመክረው የሰጠኝ መልስ በእጅጉ የሚያሳፍር ብቻም ሳይሆን የማንነቱን ሰብእና ጭምር እንድፈትሽ አጋጣሚውን ፈጥሎኛል። "እውቀቴን ላካፍል ሀገር ብዬ ብመጣ የጥልፍልፉ ብዛት አላላውስ አለኝ! እዚያው ሀገሬ ተመልሼ መሄዱ ሳይሻል አይቀርም" ብሎ ሲያማርር አድምጬው "ልክ ነህ የሀገራችን ቢሮክራሲና አገልግሎት ለማግኘት የሚኬድባቸው መንገዶች ጥልፍልፍና ውስብስብ ናቸው። አንተም እኮ ሀገር ብለህ የመጣኸው ይሄ ችግር ስላለ ተጋፍጠህ እንድታሸንፍ እንጂ፤ ችግር እየዘረዘሩ ሙሾ ለማውረድማ ሺህ ምንተ ሺህ አስለቃሾች መቼ አጣን!" ብዬ ምርር ስልበት የሰጠኝን መልስ እዚህ ዐውድ ላይ መጥቀሱ ቦታው ባይሆንም ከወዳጅነቱ ራሴን ለመለየት ግን ጥሩ ምክንያት ሆኖኛል።

ደግነቱ የልቡ ሞልቶለት ይመስለኛል፤ የተመቻቸ ወንበር ተሰጥቶት "ሹመት ያዳብር" የሚሉትን ወዳጆቹን ለማስተናገድ ሸብ እረብ ሲል ይስተዋላል። "ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ..." አለ ቀረርቶኛው የሀገሬ ሰው። ይህንን "የቀድሞ ወዳጄንና" በርካታ አስለቃሽ ሙሾ አስረጋጆችን ባሰብኩ ቁጥር የሚከተለው የተውሶ ግጥም ትዝ ስለሚለኝ እያረርኩ በለሆሳስ ደጋግሜ አነበዋለሁ፡፡፡

**"እንድ ሕዝብ ተነስቶ፤ ሙሾ አሙሺውን አስው፣**
**ወገድ ከፊታችን!**
**እኛ ስንጨነቅ ስለ እለት ኑሯችን፣**
**አንተ የምትዘፍነው ስለ ቀብራችን፤**
**ዘፈን ከሆነማ ወፏም ታዜማለች፣**
**ሙት መንፈስ ለማንቃት እየቀሰቀሰች።"**

ብለን! ብለን! ያቃተንን ስሞታ ዛሬም ኢትዮጵያ ትሰማን ከሆነ እነሆ ይድረስ ብለናል። ሙሾ አሙሺዎች በድብቅ ሳይሆን በአደባባይ፣ በስውር ሳይሆን በሚዲያ ፊት እየቀረቡ ብሶታችንን እያጋነኑ "በማር በተለወሰ አንደበት" በመቀስቀስ ዛሬም ድረስ ማስለቀሳቸውን ስላልተው ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል ባይዘናጋ ይሻል የመስለናል። ዳሩ በእነርሱ ሙሾ እዬዬ ብለን እምባችን ከብሌናችን ከረጢት ውስጥ ተንጠፍጥፎ ስላለቀ እያረርንና እየከሰልን ያለነው ደረቅ ዐይናችንን እያጨናበስን ነው።

ነፍሰ ሄሩ ደራሲያችን በዓሉ ግርማ ለካንስ የሚከተለውን እንጉርጉሮ ከትቦልን ያለፈው ቢቸግረው ነው።

**"እምባ እምባ ይለኛል፤ ይተናነቀኛል፣**
**እምባ ከዬት አባቱ፤ ደርቋል ከረጢቱ።**
**ሳቅ ሳቅም ይለኛል፤ ስቆ ሳይስቅ ጥርሴ፣**
**ስቃ እያስቀሰች መከረኛ ነፍሴ።"**

የአስለቃሾቻችን የረገዳ ተውኔት በዚህ ቁንጽል ጽሑፍ ብቻ የሚጠናቀቅ አይደለም። ብዙ የሚጻፍለት፤ ብዙም የሚነገርለት ወቅታዊ ፈተናችን ነው። ሀሳቡን ለመለኳኮፍ የተሞከረው ችግሩ ከቀን ወደ ቀን እየከፋ መሄዱ ስለሚያስደነግጠን ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር እርግጥ ነው በዓይነትም ሆነ በመጠን የሰፋ መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም። የዚያኑ ያህልም እጅግ መልካምና አጓጊ ተስፋዎች እያስተዋልንም ነው። በተለየ ሁኔታ ግን የዓለም ሀገራት ዋነኛ ችግርና ሥጋት ከስንዴ ጋር ተያይዞ የዕለት ዳቦ የማግኘቱ ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ በመጣበት በዚህ ወቅት ሀገሬ "የስንዴ ምርት ከራሷ ተርፎ ወደ ውጭ የምትልክበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን" የምሥራቹን በተግባር ማረጋገጫነት መስማት ትልቅ ደስታ እንደሆነ ለማንም የሚጠፋ አይደለም። በተለይም ርሃብና ድርቅ ሲያንገበግበን መኖሩ ብቻ ሳይሆን ለባእዳን መሳለቂያ ያደረገን ይህ ታሪክ ሊለወጥ ነው መባል በራሱ ትልቅ ብስራት ነበር።

የእኛዎቹ አስለቃሾች ግን የልባቸውንና የዐይናቸውን ብሌን አሳውረው ይህን ታላቅ የስኬት ጅማሮ ሲተቹና ሲያጥላሉ መመልከት እንግዳ አይደለም። በየአካባቢው የሚመረቁ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ማየትስ? ያስደስታል እንጂ "ደረት ጣሉና እዬዬ በሉ" አሰኝቶ የሚሟረትበት የሙሾ እንጉርጉሮ መሆን ይገባው ነበር። የኑሮን ዳገት መውጣት ተስኖን ጉልበታችን መዛሉ እውነት ቢሆንም ብዙዎቹ አስለቃሾች ግን እነርሱ ሳያለቅሱ እኛን አስለቅሰው በእምባ መራጨቱ ስለሰለቸን በሁሉም ጉዳይ ለጊዜው አደብ ገዝተው ያዘቀዘቁትን ነጠላ ቢጥሉት ይበጃቸዋል። ሟርት ሰለቸን፣ "ሆ! እያሰኙ በመንጋ መነዳቱ እጅ እጅ አለን፣ እነ እከሌን ስደቡ እየተባልን "ጃዝ መባላችን!" የሞራል ስብራት ሆነብን፣ መከራ መተረኩ አስመረረን፣ ስለዚህ አስለቃሾች ሆይ እንኳን ሳታለቅሱ ልታስለቅሱን ቀርቶ አልቅሳችሁ ለማስለቀስ ብትሞክሩም እንኳን እምባችን ስለደረቀ በከንቱ አትድከሙ። ምክንያቱም ሰለቸና። ታከተን እኮ ጎበዝ። የዳረጎት ፍርፋሪ የሚሰጧችሁ "ጌቶቻችሁም" አብልተው ስለሚንቋችሁ፣ እያጎረሱ ስለሚታዘቧችሁ ለኅሊናችሁ እንድታድሩ እነሆ ምክራችንን ተቀበሉ እንላለን። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# ኢንተርፕራይዞችን ከውጭ ኩባንያዎች ጋር የማስተሳሰር እድል የተፈጠረበት የንግድ ትርኢት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢፌዴሪ ሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፤ ምርትና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ለኢንዱስትሪ ልማት ዕድገት፣ ለሥራ እድል ፈጠራ እና ለንግድ ሥራ መስፋፋት ላቅ ያለ ድርሻ ያበረክታል የተባለለትን የኢትዮ ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ባዛር ከግንቦት 25 እስከ 29 ቀን 2014 ዓ.ም አካሂዷል፡፡ የንግድ ትርኢትና ባዛሩ የተካሄደው ‹‹የኢትዮጵያን ይግዙ- በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያድርጉ›› በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ኤግዚብሽን ማዕከል ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚታየውን መቀዛቀዝ የማነቃቃት ዓላማ የያዘው ይህ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት፣ በዋናነት የአገር ውስጥ አምራቾችን ከውጭ ከሚመጡ ኩባንያዎች ጋር በመገናኘት የልምድና የዕውቀት እንዲሁም የገበያ ትስስር መፍጠር የሚያስችል ነው፡፡ በኢግዚቢሽኑ ላይ ከኤዥያ፣ ከአፍሪካ፣ ከቱርክ፣ ከመካከለኛው ምስራቅ እስራኤል የመጡ ኩባንያዎች ተሳትፈዋል፡፡

ዓለም አቀፍ ስጋት የሆነው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መከሰቱን ተከትሎ ላለፉት ሁለት አመታት የንግድ ትርኢትና ባዛሩ በኢትዮጵያ ሳይካሄድ ቆይቷል፡፡ የተቀዛቀዘውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት የራሱን ሚና ይጫወታል በተባለው በዚህ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ በርካታ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፤ ተሳታፊዎቹ ምርትና አገልግሎታቸውን ከማስተዋወቅ ባሻገር የልምድ ልውውጥ በማድረግ በዘርፉ ያሉትን ችግሮችም ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ የቻሉበት መድረክ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የቱብራዘርስ ፉድ ኮምፕሌክስ ማርኬቲንግ ማናጀር አቶ ስሜነህ ጋሻው፤ ድርጅቱ ብስኩቶችን በተለያየ ጣዕም የሚያመርት እንደሆነ ይገልጻሉ፤ ዋፈርስ የተባለውን የብስኩት ምርት ከዚህ ቀደም ከውጭ እያስመጡ ለገበያ ያቀርቡ እንደነበር አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግን ይህን ምርት በአገር ውስጥ ማምረት ተችሏል ይላሉ፡፡ ይህም ድርጅቱን ልዩ እንደሚያደርገው ነው የሚያመለክቱት፡፡ ብስኩቱ በሀገር ውስጥ መመረቱ ለገበያ የሚቀርብበት ዋጋ ተመጣጣኝ እንዲሆን ማስቻሉን ይገልጻሉ፡፡ ከውጭ አገር ሲገባ 30 ብር ሲሸጥ እንደ ነበረ አስታውሰው፣ በፋብሪካቸው በመመረቱ በ10 ብር እየተሸጠ ይገኛል ሲሉ ያመለክታሉ፡፡ በዚህም የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት የጎላ አስተዋጽኦ አበርክቷል ነው የሚሉት፡፡

ፋብሪካው ከብስኩት በተጨማሪ መኮሮኒና ፓስታም በማምረት ለገበያ ያቀርባል፡፡ ለአብነትም በንግድ ትርኢቱ ላይ መኮሮኒ በኪሎ 55 ብር ፓስታ በፍሬ 32 ብር ሂሳብ ይዞ ቀርቧል፤ የምርቶቹ ዋጋ ውጭ ላይ ካለው ዋጋ ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ ቅናሽ እንዳለው እኛም ተመልክተናል፡፡

ለምርቶቹ በዋናነት ስንዴ እንዲሁም ቅቤዎች፣ ዘይትና ስኳር ይጠቀማል፡፡ የምርቶቹ ዋጋ በየጊዜው የሚለዋወጥ ከመሆኑም በላይ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ስሜነህ፤ ለዚህም የጥሬ ዕቃ አቅርቦት እጥረት በተለይም የስንዴ ምርት እጥረትና ውድ መሆን ያስከተለው ስለመሆኑ ይናገራል፡፡ የስንዴ ዋጋ በእጥፍ እየጨመረ ባለበት በዚህ ወቅት የምርቶቹም ዋጋ በዛው መጠን እየጨመረ ይገኛል ይላሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ህብረተሰቡ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ፓስታ መኮሮኒ መጠቀም በማዘውተሩ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት ቢኖርም፣ ፍላጎቱንና አቅርቦቱን ማመጣጠ ግን አልተቻለም፡፡ የስንዴ እጥረትና መወደድ በተለይም በፓስታና መኮሮኒ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ እያስከተለ ስለመሆኑ በመግለጽ ይህን ችግር በመፍታት በኩል እንዲህ አይነት መድረኮችም የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ እንዲህ ባሉ መድረኮች የመንግሥት አካላት የሚገኙ እንደመሆናቸው በመጀመሪያ በዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለማስረዳት ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመገናኘት የልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስችላል፡፡ በተለይም ከውጭ ከመጡ ኩባንያዎች ጋር በሚደረግ ግንኙነት የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይገኛል፡፡

ሶስተኛው ፋይዳው አምራቹና ሸማቹ በቀጥታ ተገናኝቶ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት የሚያስችለው መድረክ መሆኑ ነው፡፡ አምራቾች ምርቶቻቸውን በቀጥታ ሸማቹ ዘንድ ለማድረስና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ መንግሥት በዘረጋው የሸማቾች መስመር አማካኝነት ተደራሽ ለመሆን ፋብሪካው እየሠራ ቢሆንም፣ በቀጥታ ማህበረሰቡ ዘንድ ለመድረስ ግን የአሰራር ችግሮች እንቅፋት ሆነዋል፡፡

የአውራምባ ማህበረሰብም በዚህ አለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ላይ የኑግ ዘይትና የተለያዩ ባህላዊ አልባሳት ምርቶችን በስፋት ይዘው ቀርበዋል፤ የማህበረሰቡ የሽያጭ ባለሞያ ወጣት ምትኩ ታረቀኝ እንዲህ ያሉ መድረኮች የጎላ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይናገራል፤ አልባሳቱ በሙሉ በሸመና የተሠሩ የእጅ ሥራ ውጤቶች መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ከአንገት ልብስ ጀምሮ ነጠላ፣ ኩታ፣ ጋቢ፣ ጋዋን፣ ቁምጣና ቲሸርት፣ መጋረጃና የአልጋ ልብሶችን ጨምሮ በጠቅላላው 40 አይነት አልባሳትን ይዞ መቅረቡን ያብራራል፡፡

አውራምባ ማህበረሰብ የዘይት ፋብሪካ እንዳለው ጠቅሶ፣ ከዚህም ንጹህ የተጣራ የኑግ ዘይት በብዛት ይዞ መቅረቡን ይጠቁማል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለዘይት ግብአትነት የሚውለው ሱፍ ዋጋው በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መምጣትን ተከትሎ በዘይት ዋጋ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ መታየቱን ወጣት ምትኩ አያይዞ ይገልጻል፤ አንድ ሌትር ዘይት በብር 220 ብር፣ አምስት ሌትሩ ደግሞ 1100 ብር እየተሸጠ መሆኑን አስረድቷል፡፡

‹‹ አምራቾች ምርታቸውን አውጥተው ለሸማች ማቅረብ የሚችሉበትና ምርቱም የሚተዋወቅበት አንዱ መንገድ እንዲህ ያለው መድረክ ነው›› በማለት መሰል የባዛር ገበያዎች ያላቸውን ፋይዳ ይናገራል፡፡ ምርት ሸማቹ ዘንድ ካልደረሰ ይኑር አይኑር እንደማይታወቅ ጠቅሶ፣ እንዲህ ባሉ ሰፊ መድረኮች ተሳታፊ መሆን ደግሞ ምርቶቹን በቀጥታ ለሸማቹ ከማቅረብ ባለፈ የልምድ ልውውጥና የገበያ ትስስር ለመፍጠር ይበልጥ ምርታማ ለመሆን እንደሚያግዝ ነው የሚናገረው፡፡

በንግድ ትርኢቱ ላይ የተገኙት የኢንዱስትሪ ልማት ኮርፖሬሽኑ አቶ ሙሉጌታ ከበደ በበኩላቸው በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ላይ ለማስተዋወቅ በመድረኩ ተገኝተዋል፤ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ሼድ ወስደው መሥራት እንዲችሉ የማስተዋወቅ ስራ መስራታቸውን ነው አቶ ሙሉጌታ የተናገሩት፡፡

በተለያየ ዘርፍ የተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በተለይም በቆዳ፣ በጨርቃጨርቅ፣ በሳሙናና በሌሎችም ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው ማምረት የሚችሉበትን ዕድል ለመፍጠር መሰል መድረኮች ወሳኝ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

እንደ አቶ ሙሉጌታ ገለጻ፤ ኢንተርፕራይዞቹም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው ማምረት ቢችሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ ፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ፋይዳ በዋናነት ሰላማዊና የተጠናከረ ጥበቃ ያላቸው መሆናቸው ላይ ነው፡፡ ማንኛውንም መንግሥታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል በቅጥር ግቢ ውስጥ ያገኛሉ፡፡ የውሃ፣ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክና ሌሎችም መሰረተ ልማቶች የተሟላላቸው እንደመሆኑ እዛ ሲገቡ በተሻለ መጠን ማምረት ይችላሉ፡፡

‹‹የንግድ ትርዒቱ የገበያ ትስስር በመፍጠር በኩልም የጎላ አስተዋጽኦ ያበረክታል›› ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራቾች ምርቶቻቸውን በኤግዚቢሽኑ ላይ ይዘው በመቅረብ ምርቶቹን ለሚፈልግ ማንኛውም ኩባንያም ሆነ ነጋዴ ማስተዋወቃቸውን ይገልጻሉ፡፡ በንግድ ትርኢቱ ላይ የተገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኩባንያዎች እንደ መድሃኒት፣ ቀለም፣ ክርና የመሳሰሉትን ምርቶች ይዘው ቀርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከመደበኛ ተግባራቶቹ መካከል አንዱ ንግድና ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ነው፤ ከዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ጋር በቀጥታ በመገናኘት አገራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችል ተግባር ያካሂዳል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠባባቂ ዋና ጸሃፊ አቶ ውቤ መንግሥቱ፤ በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ላለፉት ሁለት ዓመታት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ አለመካሄዱን አስታውሰው፣ የንግድ ትርዒቱ በአሁኑ ወቅት ተቀዛቅዞ ያለውን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ከፍተኛ ድርሻ አለው ይላሉ፡፡

እንደ አቶ ውቤ ገለጻ፤ የኢትዮጵያን ይግዙ የሚለው መሰረተ ሀሳብ ሰፋ ያለ መልዕክት ያለው ሲሆን የኢትዮጵያን ምርት ስንገዛ የኢትዮጵያ አምራቾችን ማበረታታትና ማስፋት ይቻላል፡፡ አምራቾች ሲስፋፉ ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ጀምሮ የተሻለ ገበያ በማግኘት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡ በአገር ውስጥ ምርት መጠቀም ባህልን በማሳደግ ለውጥ ማምጣትም ይቻላል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የገበያ ጥናት ዳይሬክተር አቶ ዘርይሁን አለማየሁ፤ የንግድ ትርኢቱ ተሳታፊ ኢንተርፕራይዞች ከሁሉም ክልሎች የመጡ ናቸው፤ የቦታ ኪራይ የሌለባቸው በመሆኑም ምርቶቻቸውን ከማስተዋወቅ ባለፈ ለህብረተሰቡ በሚያስተዋውቁበት ዋጋ ለሽያጭ ማቅረብ መቻላቸውን ይገልጻሉ፡፡

አምራች ኢንተርፕራይዞቹ በኤግዚብሽንና ባዛር ውስጥ ለሚጠቀሙት ቦታ ክፍያ ቢጠየቁ ምርት ዋጋ ላይ ተጨማሪ ዋጋ ሊጠይቁ ስለሚችሉ የዋጋ ውድነት ይከሰታል፡፡ ነገር ግን ከክፍያ ነጻ የገበያ ቦታ መፈቀዱ ምርቶቻቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ ለማቅረብ ያስችላቸዋል፡፡ በንግድ ትርኢቱ የገበያ ዕድል የተፈጠረላቸው የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ላይ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያዎች ይዘው ሲቀርቡ የማስተዋወቅና የገበያ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡ አቅም ካላቸው ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ጥምረት በመፍጠር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁትን የማምረቻ መሳሪያዎች እንዲሁም ካፒታል አቅም ችግርንም ጭምር በጋራ ጥምረት ፈጥረው መሥራት እንዲሁም ትስስር ፈጥረው መጓዝ እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ጋር በመተባበር ተሳታፊ ሆነው አቅማቸው እንዲዳብር የሚያስችል ሥራ እየሠራ መሆኑን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡ በንግድ ትርኢቱ ላይ በዋናነት በአምራች ዘርፉ የሚገኙ እንደ ጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ የባልትና ምርቶችና የንጽህና መስጫ ሳሙናዎች እንዲሁም የግብርና ምርት ሆነው እሴት የተጨመረባቸውና የተቀነባበሩ ምርቶች ማቅረባቸውን ያብራራሉ፡፡

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ድጋፍ የሚደረግላቸው ሆነው ከአካባቢና ከክልል በላይ የማቅረብ አቅም ያላቸው፤ ለአገር ውስጥ ገበያ ተደራሽ የሆኑ፤ በቀጣይም ለውጭ ገበያ ማስተዋወቅ ይችላሉ የተባሉ ኢንተርፕራይዞች ተመርጠው በንግድ ትርኢቱ እንዲሳተፉ መደረጉን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፣ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ከ50 በመቶ በላይ ሴቶች ተሳታፊ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ባዛሩ በዋናነት ማስተዋወቅ ላይ ማተኮሩን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ከሌሎቹ የንግድ ትርዒቶች ለየት ባለ መንገድ ባዛርም የተፈቀደ በመሆኑ 62 የሚደርሱ ኢንተርፕራይዞችን ተሳታፊ ሆነዋል ይላሉ፡፡ በዚህም ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር የገበያ ትስስር እንደሚፈጠር ነው ያስታወቁት፡፡ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር የአቻ ለአቻ ግንኙነት መፍጠር እንዲቻል ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራቱን ይገልጻሉ፡፡ በቀጣይ ኢኮኖሚ የበለጠ ለማነቃቀት ‹‹የኢትዮጵያን ይግዙ፤ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያድርጉ›› በሚለው መርህ ህብረተሰቡ በአገር ውስጥ ምርት እንዲጠቀምም ጠይቀዋል፡፡

ዳይሬክተሩ በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ባዛሩ ላይ 54 ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ በማድርግ የዕቅዱን 87 በመቶ ማሳካት መቻሉን ተናግረዋል፡፡ ኢንተርፕራይዞቹ በአምስቱ ቀናት በስፋት ምርትና አገልግሎታቸውን በማስተዋወቅ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር የእርስ በእርስ ትውውቅ የማድረግ ዕድልም እንደተፈጠረላቸውም ነው ያመለከቱት፡፡ በዚህም ምርትና አገልግሎቶችን በተሻለ ደረጃ ማስተዋወቅና ለገበያ ማቅረብ እንደሚቻል ዕውቀት ገብይተዋል ይላሉ፡፡

የንግድና ባዛሩ ዋና ዓላማ ምርትና አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ እንደመሆኑ ይህን ማሳካት ተችሏል ያሉት አቶ ዘርይሁን፣ በቀጣይም ኢንተርፕራይዞች ከአገር ውስጥ ገበያ ባለፈ በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉበትን ዕድል ለማስፋት እየተሰራ መሆኑንም ይጠቁማሉ፡፡ ኢንተርፕራይዞቹም በምርት ጥራት፣ በአቅርቦትና በዋጋም ጭምር ተወዳዳሪ በመሆን ከኤግዚብሽንና ባዛር ውጭም በዲጅታል የግብይት ዘዴዎች በመጠቀም ምርትና አገልግሎታቸውን የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

> **በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ባዛሩ ላይ 54 ኢንተርፕራይዞች የተሳተፉ ሲሆን፣ በዚህም የዕቅዱን 87 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ ኢንተርፕራይዞቹ በአምስቱ ቀናት በስፋት ምርትና አገልግሎታቸውን በማስተዋወቅ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር የእርስ በእርስ ትውውቅ የማድረግ ዕድልም ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ምርትና አገልግሎቶችን በተሻለ ደረጃ ማስተዋወቅና ለገበያ ማቅረብ እንደሚቻል ከንግድ ትርኢቱ ዕውቀት ገብይተዋል፡፡**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ችግር ብልሃትን ይወልዳል

**ዋስልኝ አየለ**

እነሆ ዛሬ ሰኔ አንድ ብለን የክረምቱን ወራት ጀምረናል። በኢትዮጵያ የወቅቶች ምደባ የክረምት ወር የሚጀምረው በሰኔ ነው። ሰኔ፣ ሐምሌ እና ነሐሴ ማለት ነው።

የክረምት ወቅት ደግሞ ለኢትዮጵያ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። ክረምት ማለት ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚያችን ዋልታና ማገር የሆነው የግብርና ሥራ የሚሰራበት ነው።

የዛሬው የክረምት መግባት ያስታወሰኝ ታዲያ የገበሬውን ሕይወት ነው። የገበሬውን ሕይወት ሳስታውስ ባለፉት ሳምንታትና ወራት ‹‹ምግቤን ከጓሮዬ›› በሚል በመንግሥት ደረጃ የተጀመረው የከተማ ግብርና ትዝ ያለኝ።

‹‹ምግቤን ከጓሮዬ›› በሚል በመንግሥት ደረጃ የተጀመረው የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በአንዳንድ ወገኖች ሲተች ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ‹‹የትኛውን ትርፍ ቦታ ነው አትክልት የምንተክልበት›› የሚል ነበር። በመንግሥት በኩል ይባል የነበረው ደግሞ በተለያዩ መገልገያ ዕቃዎች መጠቀም እንዳለብን ነው።

ለዚህ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ ገበሬውን ነው ምሳሌ ማድረግ ያለብን። እርግጥ ነው ገበሬ ከዚህ ቀደም በመገልገያ ዕቃዎች ላይ አልጀመረም፤ ዳሩ ግን የእጅ መዳፍ የምታክል መሬትን እንዴት እንደሚጠቀማት ማየት ችግር ብልሃትን እንደሚወልድ ያሳያል።

በገጠር አካባቢ አሁን አሁን የእርሻ መሬት እየተወደደ ነው። ትልልቅ አባቶች የአሁን ወጣቶችን እያዩ ይገረማሉ። የሚገረሙበት ምክንያት፤ ቀደም ሲል ለእርሻ የማይውለውን መሬት ለእርሻ ሲያውሉ አይተው ነው። ቀደም ሲል በነበረው ዘመን የሚታረሰውና የማይታረሰው መሳ ለመሳ (እኩል) ነበር፤ እንዲያውም የማይታረሰው ሊበልጥ ይችላል። አሁን ግን እንደዚያ ብሎ ነገር የለም፤ የእግር መርገጫ የምታክል መሬት ሳትቀር ገበሬዎች እየፈቀፈቁ ያርሷታል።

‹‹ይህ ለምን ሆነ?›› ከተባለ፤ ችግር ነው ያስተማራቸው። ወጣቱ ገበሬ የእርሻ ማሳ ሲጠበው የፈጠረው መላ ነው። አባት ገበሬ መሬት ለልጁ አካፍሎ ሲጠበው ችግር ያመጣለት ዘዴ ነው። ቀደም ባሉት ዘመናት ከመኖሪያ ቤት አቅራቢያ ላይታረስ ይችል ነበር፤ አሁን ግን እስከ ቤቱ አጠገብ ድረስ ይታረሳል። እንደመሬቱ ባህሪ የሚስማማውን እህል ይዘራል ማለት ነው። ይህ ለምን ሆነ ከተባለ ችግር የወለደው መላ ነው።

በነገራችን ላይ ‹‹የሥልጣኔ ምንጩ ችግር ነው›› ነው የሚባለው። የሰው ልጅ ዋሻ ውስጥ ይኖር ከነበረበት ዘመን አንስቶ እስከ ዛሬው ረቂቅ ዓለም ድረስ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን አሳይቷል። እነዚህን ሥራዎች የፈጠራቸው ችግር ነው። ግዑዝ አካላትን አፋጭቶ እሳት ከመፍጠር እስከ ኤሌክትሪክ ድረስ፣ በእንስሳት ጀርባ ከመሄድ በሰማይ የሚበር አውሮፕላን እስከ መፈልሰፍ የደረሰው ችግር እያስተማረው ነው።

አንዷት የቅርብ ምሳሌ ብቻ እንውሰድ። ኮቪድ-19 በዓለም ብሎም በአገራችን ሲከሰት ከፍተኛ ጭንቀት ነበር። ቫይረሱ በእጅ ንክኪ እንደሚተላለፍ ሲታወቅ በእጅ መነካካት አስፈሪ ሆነ። ይህ ችግር ቀደም ሲል በእጅ እየከፈትን እንታጠብ የነበረውን ልማድ የሚያስቀር ዘዴ ወለደ። ይህን ዘዴ ለብዙ ዓመታት አላሰብነውም ነበር። ግን ችግር ብልሃትን ይወልዳል ስለሚባል ሲጨንቀን ያንን ዘዴ ፈጠርን። እርግጥ ነው ሁሉም ሰው እንዲህ አይነት ዘዴ ይመጣለታል ማለት አይደለም፤ ጥበብና ማስተዋልን ይጠይቃል።

ስለዚህ የከተማ ግብርና ችግር የወለደው ዘዴ ነው። አዎ! በበሬ ወይም በትራክተር የሚታረስ ሰፊ መሬት ቢኖር ጥሩ ነበር፤ ግን የለም! ስለዚህ መሬትም ምግብም እንጣ? እንዲህ አይነት ችግር ሲያጋጥም ችግሩን የምንወጣበት ዘዴ እንፈልጋለን ማለት ነው። የመገልገያ ዕቃዎች ውስጥ አፈር እያደረግን በየግድግዳውና አጥሩ ላይ እንሰቅላለን ማለት ነው። ከገበሬው ማሳ እንደሚታረሰው በኩንታል የሚታፈስ ምርት ባናመርትም የዕለት ምግብ ማምረት ይቻላል ማለት ነው።

ችግሩ ግን አዲስ ነገር በተጀመረ ቁጥር ማጣጣል ይቀናናል። የማይቻልና መሆን የሌለበት ነገር አድርገን ነው የምናየው። የእርሻ መሬት ችግርን ለመቅረፍ መፍትሔው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መጠቀም እንጂ ማጣጣል አይደለም።

እዚህ ላይ ግን መንግሥትም አንድ ልብ ማለት ያለበት ነገር አለ። በቤትና በጓሮ ውስጥ በመገልገያ ዕቃዎች ላይ የሚተከል አትክልት ችግር ፈቺ አይደለም። በሄክታር የሚቆጠር ሰፋፊ መሬት በፀጥታ ችግር ምክንያት ከእርሻ ውጭ ነው። በዋናው ጦርነትም ሆነ በአካባቢያዊ ሽፍቶች የተፈናቀሉ ብዙ ገበሬዎች አሉ። እነዚህ ገበሬዎች ወደ ከተማ እየተሰደዱ ለልመና ተዳርገዋል። አርሶ የሚያበላው ወገን እየተፈናቀለ በጣሳ እና በፕላስቲክ የሚተከል ጎመን ችግርን አይቀርፍም።

‹‹ምግቤን ከጓሮዬ›› የከተማ ግብርና ከአንዳንድ ወገኖች ትችት ያገጠመው ዋናው አምራች ገበሬ ሁኔታዎች ይመቻቹለት በሚል ነው። ምክንያቱም በአገር ደረጃ ያለው ችግር የሚቀረፈው በተለመደው በበሬም ሆነ በዘመናዊው ትራክተር በሚታረሰው እንጂ ግድግዳ ላይ በሚንጠለጠል የውሃ ፕላስቲክ አይደለም። ስለዚህ መንግሥት ለዋናው አምራች ገበሬም ከፍተኛውን ትኩረት መስጠት አለበት።

ምናልባት አሁን የተጀመረው ሕግ የማስከበር እንቅስቃሴ ይህን ችግር ይቀርፍ ይሆናል። ከዚያ በፊት ግን በብዙ አካባቢዎች ገበሬው የእርሻ ማሳውን ለሽፍታ እየለቀቀ ወደ ከተማ ቦታ ሲገባ ነበር። አዲስ አበባ ውስጥ በየትኛውም አቅጣጫ ብትወጡ በየመስመሩ ዳር እጁን ለልመና የዘረጋ ገበሬ ነው የምታዩት። ይሄ ገበሬ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታ የሆነው የግብርና መሰረት ነበር። ስለዚህ ሁኔታዎች ተመቻችተውለት ቶሎ ወደ እርሻው መመለስ አለበት። ለአገር የሚበቃው ገበሬ እጁን ለልመና ዘርግቶ በፕላስቲክ በጣሳ በሚተከል የጓሮ አትክልት ብቻ ኑሮን ማሻሻል አይቻልም።

ስለዚህ መሆን ያለበት ሁለቱም ነው። ገበሬው በሰፊው ይረስ፣ የከተማ ነዋሪው ደግሞ ያለችውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም በትንሹም ቢሆን ራሱን ይቻል። እንደዚያ ከሆነ ችግርን በጋራ መጋፈጥ ይቻላል ማለት ነው። ገበሬው ለልመና ከተዳረገ፣ የከተማው ነዋሪ በገበሬው ላይ ጥገኛ ሆኖ ከቀረ፤ ተያይዞ መውደቅ ሆነ ማለት ነው።

ቀደም ሲል እንዳልነው ችግር ነው ብልሃትን የሚያስተምረው። ለምሳሌ ቤታችን ሰፊ ሲሆን እና ጠባብ ሲሆን የቤት ውስጥ ዕቃ አቀማመጣችን ይለያያል። ቤታችን ሰፊ ከሆነ፤ እያንዳንዱ ዕቃ ራሱን ችሎ ይቀመጣል። ጠባብ ሲሆን ግን አንዱን በአንዱ ላይ እያነባበርን እናስቀምጣለን። በሥርዓት በሥርዓት እንደረድራቸዋለን። ለዕቃዎቹ አቀማመጥም ምቹ ይሆናል ማለት ነው። በሰፊ ቤት ውስጥ ግን በቂ ቦታ ስላለ በሥርዓት ከመደርደር ይልቅ ያገኘንበት እንጥለዋለን።

የእርሻ ቦታዎችም ልክ እንደዚሁ ነው። ሰፊ የእርሻ ማሳ በነበረበት ጊዜ የአረምና ድንጋይ መጣያ ይበዛል። የእርሻ ማሳው ጠባብ ሲሆን ግን እርከን ይሰራሉ፤ ድንጋዩ በሥርዓት ይደረደራል፤ አረምና ሌሎች ነገሮችም በሥርዓት ተለቅመው አንድ ቦታ ብቻ ይቀመጣሉ።

አጠቃላይ የጓሮ አትክልት ‹‹ችግር ብልሃትን ይወልዳል›› በሚለው ነውና እንልመደው!

# ዓለም አቀፍ



## ዩኬ ረዥም ርቀት ተወንጫፊ ሚሳኤሎችን ለዩክሬን ልትሰጥ ነው

ዩናይትድ ኪንግደም ለመጀመርያ ጊዜ ኤም 270 የተባሉ ረዥም ርቀት ተወንጫፊ ሚሳኤሎችን ለዩክሬን ልትሰጥ ነው።

ዩኬ እነዚህን እጅግ ዘመናዊ ሮኬት ማስወንጨፍያ መሣሪያዎች መቼ እና በምን ያህል መጠን ወደ ዩክሬን እንደምትልክ አልገለጸችም።

ሆኖም ቢቢሲ ያገኘው መረጃ ለመነሻ ያህል ሦስት ሚሳኤል ማስወንጨፍያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ዩኬ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰችው ከአሜሪካ ጋር ከመከረች በኋላ ነው።

የሩሲያው ቭላድሚር ፑቲን አሜሪካ ለዩክሬን የምትሰጠው የጦር መሣሪያ ብዙ እንዳስቆጣቸው ተሰምቷል።

ትናንት እሑድ ፑቲን እንደተናገሩት አሜሪካ ይህን የጦር መሣሪያ ልገሳ የማታቆም ከሆነ ሩሲያ በዩክሬን የምታደርሰው ጥቃት መጠኑ እየሰፋ እንደሚመጣ ዛቻ ሰንዝረዋል።

ዩኬ ይህን ውስብስብና ዘመናዊ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ለዩክሬን ወታደሮች በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ስልጠና እሰጣለሁ ብላለች።

አሜሪካ ባለፈው ሳምንት ነበር ኤም142 ተወንጫፊ ሚሳኤል ሲስተምን ወደ ዩክሬን የላከችው።

አሜሪካ ይህን ረዥም ርቀት ተወንጫፊ መሣሪያ ብትሰጥም ዩክሬን ይህን መሣሪያ ወደ ሩሲያ ግዛት እንዳትተኩስ በማሳሰብ ነው።

አሁን ከዩኬ ለዩክሬን የሚለገሰው ኤም270 ሮኬት ሲስተም 300 ኪሎ ሜትርየሚወነጨፍ ሲሆን በአንድ ደቂቃ 18 ዙር ሮኬት ሊያስወነጭፍ ይችላል።

25 ቶን የሚመዝነው ይህ ሮኬት በሰዓት 64 ኪሎ ሜትር በመክነፍ የጠላትን ኃይል መምታት የሚችል ነው።

ፑቲን ትናንት ከአገሪቱ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጋር በነበራቸው ቃለ ምልልስ ምዕራባዊያን ለዩክሬን መሣሪያ በገፍ እየለገሱ ያሉት ይህን ጦርነት በተቻለ መጠን ቶሎ እንዳይጠናቀቅ ለማድረግ ነው።

ሩሲያ ከኪየቭ ወደ ምሥራቅ ዩክሬን ዶንባስ ግዛት ትኩረቷን ካደረገች ወዲህ ትናንት እሑድ ለመጀመርያ ጊዜ ኪየቭ ላይ ጥቃት ሰንዝራለች።

## የአውሮፓ ሕብረት ለተፈጠረው የምግብ ቀውስ ሩሲያን ተጠያቂ በማድረጉ ክሬምሊን ስብሰባውን ረግጣ ወጣች




ሩሲያ በዩክሬን የፈፀመችው ወረራ ለዓለም አቀፍ የምግብ ቀውስ መንስኤ ሆኗል ሲሉ የአውሮፓ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት በመውቀሳቸው ምክንያት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሩሲያ አምባሳደር የፀጥታው ምክር ቤት ስብሰባን ረግጠው ወጥተዋል።

ሩሲያ የምግብ አቅርቦቶችን እንደ “ሚሳኤል” በመጠቀሟ ሕዝብን ወደ ድህነት እያስገባች ነው ሲሉ ቻርለስ ሚሼል ገልጸዋል።

የሩሲያው ተወካይ ቫሲሊ ኔቤንዚያ በበኩላቸው ሚሼል የውሸት መረጃ አሰራጭተዋል ሲሉ ከሰዋል።

በጦርነቱ ምክንያት የምግብ እህል ከዩክሬን ወደቦች እንዳይነሳ እንቅፋት ሆኗል።

ዩክሬን የምግብ ዘይትን ጨምሮ እንደ በቆሎ እና ስንዴ ያሉ ጥራጥሬዎችን ወደ ውጭ በመላክ ቀዳሚ ከሆኑ አገራት አንዷ ናት።

ሩሲያ በበኩሏ ከፍተኛ መጠን ያለው እህል እና ማዳበሪያ ወደ ውጭ ትልካለች። የእነዚህ ምርቶች እጥረት ለዋጋ ጭማሪ ምክንያት ሆኗል።

ሚሼል በኒውዮርክ በተካሄደው የፀጥታው ምክር ቤት ስብሰባ ላይ “የተከበሩ የሩሲያ ፌዴሬሽን አምባሳደር፣ እውነታውን እንነጋገር ከተባለ ክሬምሊን የምግብ አቅርቦቶችን እንደ ስውር ሚሳኤል በታዳጊ አገራት ላይ እየተጠቀመችበት ነው” ብለዋል።

“የሩሲያ ጦርነት ያስከተለው ዳፋ በዓለም ዙሪያ እየደረሰ ነው። ይህም የምግብ ዋጋን ከማናር ባለፈ ሰዎችን ወደ ድህነት በመግፋት በተለያዩ አካባቢዎች አለመረጋጋት እያስከተለ ነው” ብለዋል።

“ለዚህ የምግብ ችግር ብቸኛዋ ተጠያቂ ሩሲያ ናት።“

በሩሲያ በተከለከለው የባሕር ኃይል እገዳ ምክንያት በዩክሬኗ ኦዴሳ ወደብ በሚሊዮን ቶን የሚቆጠር እህል ተከማችቶ ማየታቸውን ተናግረዋል።

ሚሼል አክለውም ሩሲያ በምታደርገው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ምክንያት እህል ከመሰረቅ ባለፈ በዩክሬን ሰብል እንዳይዘራ እና እንዳይሰበሰብ አድርጋለች ሲሉ ከሰዋል።

ይህ አስተያየታቸው ኔቤንዚያን ስብሰባውን ረግጠው እንዲወጡ አድርጓቸዋል። “እውነቱን ላለመስማት ቀላል በመሆኑ ስብሰባውን ረግጠው ሊወጡ ይችሉ ይሆናል” ሲሉ ሚሼል በቀጥታ ለአምባሳደሩ ተናግረዋል።

ኔቤንዚያ ከወጡ በኋላ ለሮይተርስ እንደተናገሩት “ቻርለስ ሚሼል ለማሰራጨት በመጣው ውሸት” ምክንያት መቆየት እንዳልቻሉ ተናግረዋል።

በሌላ ስብሰባ ላይ ደግሞ የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን ሩሲያ የዩክሬን እህል ከአገሪቱ እንዳይወጣ እየከለከለች መሆኑን ገልጸዋል።

የሩሲያ ጦር የዩክሬንን የእርሻ መሠረተ ልማትን አውድሟል ሲሉም ከሰዋል።

ከበጎ አድራጊዎች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከግሉ ሴክተር አካላት ጋር በበይነ መረብ ባደረጉት ስብሰባ ወቅት ነው ብሊንከን “በኦዴሳ አቅራቢያ ወደ 20 ሚሊዮን ቶን የሚጠጋ ስንዴ አለ። እህል የተሞሉ መርከቦችም በሩሲያ እገዳ ምክንያት ቆመዋል” ብለዋል።

ከሚሼል ጋር በሚስማማ መልኩም ሩሲያ የዩክሬንን እህል ለራሷ ጥቅም ለመሸጥ “ትዘርፋለች” የሚሉ ታማኝ ዘገባዎች መኖራቸውን ተናግረዋል።

**ምንጭ ቢቢሲ**

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ስለኢትዮጵያ እውነቱን የመሰከረችው ድሩሲላ

ግርማ መንግሥቴ

ዛሬ ከነበርንበት፣ የራሳችንን ባለውለታዎች ከምንዘክርበት አካሄድ ለጊዜውም ቢሆን ወጣ እንበልና ከውጪው አለም ለኛ ሲሉ፣ ለኢትዮጵያ ሲሉ ያልሆኑት የሌላቸውን፣ ድሩሲላ ዱንጂ ሂውስተንን የመሳሰሉትን (በተለመደው አገላለፅ፣ "የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ወዳጆች" የምንላቸውን) በማንሳት ልፋትና ስለ ኢትዮጵያ የነበራቸውን ስሜትና ራዕይ እንጋራ።

የዛሬዋ የ"ባለውለታዎቻችን" ተስተዋሽ፣ ምናልባትም ይህ ጸሐፊ "ከኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ወዳጆች መካከል ሰው ጥራ" ቢባል ቁጥር 1 ላይ የሚያስቀምጣት የብዕር አርበኛ ስትሆን፤ ምክንያቱም አርበኝነቷ ከብዕር፣ እምነቷም ከእውነት፣ ማስረጃዎቿም ከመረጃ የመነጩ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ ርእሷም ሆነ ርእሰ-ጉዳይዋ ኢትዮጵያና የጥቁር ሕዝቦች የጋራ ማንነት መሆኑ ነው።

በአካዳሚው ደብርም ሆነ አድናቂዎቿ ዘንድ "ራሷን በራሷ ያበቃች የታሪክ ተመራማሪ፣ ጋዜጠኛ፣ መምህር፣ ሙዚቀኛ ...፤ በአሜሪካ የአፍሪካን-አሜሪካን ስርአተ ትምህርት ውስጥ በአዘጋጅነት፣ በተለይም "The Wonderful Ethiopians." በሚለው ማስተማሪያ ቴክስት አርቃቂነት የተሳተፈች፤ አድር ባይ ብዕርን ሁላ ያስተነፈሰች አፍሪካ-አሜሪካዊቷ ድሩሲላ ..." በሚል የምትታወቅ፤ ግዙፍ ሰብእና ያላትና ስራዎቿ ለምእተ አመት አራት ፈሪ በሆነው በዚህ እድሜያቸው እንኳን ገበያውን ከመምራት ያልቦዘኑላት ሰው ነች።

"የአፍሪካ ሕዝብ ምንም አይነት ታሪክ የሌለው፤ ያልሰለጠነ ..." የሚለውን የነጮች ዘረኛ አስተሳሰብን አምርሮ በመቃወም በአፍጢሙ የሚደፋው (ልክ የአድዋው ድል እንዳደረገው)፣ ዱቦይስ (W.E.B. DuBois) "The Negro" (1915) ስራ በጎ ትፅእኖ ስር የወደቀችው ድሩሲላ፤ በኢትዮጵያ ማንፀሪያነት በአጠቃላይ የጥቁር ሕዝብን ማንነት የተመለከቱ ሶስት (መጽሐፍ I (Book I), መጽሐፍ II, መጽሐፍ III) ስራዎቿን (Peggy Brooks-Bertram ከዚህኛው በተጨማሪ ሌሎች ስድስት ስራዎች (ሁሉም ከ1915 እስከ 1926 ባለው ጊዜ ውስጥ የተፃፉ) አሏት፤ የሁለተኛ ቅፅ ርእስም "Origin of Civilization from the Cushites" ነው፤ ይህም በ1998 ተገኝቷል ነው የሚሉት) ስትሰራ ያለምንም የከፍተኛ ትምህርት ዲግሪ፣ ያለ ምንም የገንዘብ እርዳታና ረዳት ... ነበር። (Thabiti Asukile በ"Drusilla Dunjee Houston (1876-1941)", (February 12, 2007)፤ Brooks-Bertram (2002, xlii)ም ዛሬ እንዲህ እንደ ቀልድ የተዘነጋችው ድሩሲላ በነበረችበት ወቅት በኦክላሆማ ማንም የማይደርስባት ማህበረሰብ አንቂ፣ አስተማሪ፣ የተዋጣላት ደራሲ ... ነበረች በማለት መዘንጋት የለባትም ከሚል ቁጭት ጋር ማንነቷን ይገልፃሉ።

በተለይም "ክላሲክ" የተባለውን፣ እኛ ዛሬ እዚህ ድሩሲላን በባለውለታነት እናነሳ ዘንድ ምክንያት የሆነን ዘላለማዊ ስራዋ (መጽሐፍ I)ን ተከትሎ የጎረፈላት አድናቆት ለማመን ከሚቻለው በላይ ሲሆን፤ የስራው ተወዳጅነትም ሆነ ተጠቃሽነት (Reference) እስከዛሬም እየጨመረ እንጂ ሲቀንስ አልታየም። ይህ ስራዋ በብዙዎች "እፀብ ድንቅ" የተባለላት (Thabiti Asukile) ሲሆን፤ በአድናቆት ላይ አድናቆትን ሁሉ አትርፎላት ዝናዋ ይናኝ፤ በተለይም በጥቁር ሕዝቦች፤ በምሁራንና ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ዘንድ አግራሞትና አድናቆት፤ በነጮቹ ዘንድ የልብ መሸበርና የወኔ መራድ፤ የስሜት መሸርሸር፣ የስነልቦና ድቀት ... ሁሉ ይፈጠር ዘንድ ምክንያት ሆኗል።

የጥቁር ሕዝቦችን መብቶች የተመለከቱ፤ ፀረ-ዘረኝነት አቋምን የሚያራምዱ ከ3ሺ በላይ ርእሰ አንቀፆችን የጻፈችበት የ"Oklahoma Black Dispatch" ጋዜጣ ኤዲተር የነበረችው በዘመኗ ድምጽ ሌላቸው ሴቶች ልሳንና የተዋጣላት ሞዴል (quintessential race woman) የነበረችው ድሩሲላ ስራዋ አሉ የተባሉ የዓለም ምሁራንን ሁሉ ፈትኗል፤ እጃቸውን አፋቸው ላይ አስጭኖም ጉድ አስብሏል። የኋላ ኋላ፣ ሳይወዱ በግድ እውነቱ ይቀበሉ ዘንድ አስገድዷቸዋል። ይገደዱ እንጂ፣ በተለይ የነጭ የበላይነት ሰባኪ ምሁራን ስራዎቿን "የተጋነነ" በሚል ከማጣጣል ባለፈ ተራ ዘለፋ ውስጥ እስከመግባት ድረስ ሄደው እንደነበር በታሪክ ሰፍሮ ይገኛል። አይውጡት አይተፉት ነገር ሆኖባቸው፤ የተጠቀመቻቸው ሰነዶችና ያቀረበቻቸው መረጃና ማስረጃዎች እማይወለዱ ሆነው እንጂ ስራዎቿን በነጭ ቢሰረዙት በወደዱ ነበር።

ይህንን አለምዓቀፍ የኃይማኖት እና ሰብአዊ እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ስመ-ጥር ቤተመጻሕፍት፤ የዘርፉ ልሂቃን እስካሁን ድረስ በስስት የሚያዩትና ከጓዳ ይወጣ ዘንድ እማይፈቅዱት ስራዋን ... ነጮችን ለማበሳጨት፤ ጥቁሮችን ለማስደሰት ሳይሆን ዘረኝነትን በመቃወም እውነቱን ለአለም ለማሳየት ነው የጻፍኩት ያለችለት ይህ፣ ለ100 አመት አራት ፈሪ የሆነው ስራዋ ከላይ በጠቃቀስናቸው በጣም ጥቂት አድናቆቶች ብቻ ተወስኖ የቀረ አይደለም። ይልቁንም፣ በኦንላየን (አማዞን) ገበያ ላይ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ እንኳን ብንመለከት በአሁኑ ሰአት፣ ገበያውንም እየመራ ያለው ይኸው በተለያየ የህትመት ደረጃ/ጥራት ለገበያ የቀረበው የ100 አመቱ "መጽሐፍ I" (ጌታቸው ተስፋዬ ጎጂ በተባሉ ሰው "ፒራሚድ ገንቢዎቹ ጥንታዊ ኢትዮጵያዊያን!" (2002 ኢ.ም) በሚል ርዕስ ተጎራርዶ ተተርጉሟል)፣ በከፍተኛ ዋጋ ($62) እየተቸበቸበ የሚገኝ ሲሆን፤ "ምድር አንቀጥቅጥ" ላልነው ማሳያችን ደግሞ መጽሐፉ ከአስር አመት በፊት በሕዝብ ጥያቄ እንደገና እንዲታተም ሲጠየቅ፣ ባልተለመደ፣ የአሜሪካ መንግሥት የእስከ ዛሬ አቋም ባልሆነ ሁኔታ "አይቻልም" በሚል መከልከሉና የአንድ ሰሞን መነጋገሪያ መሆኑ ነው።

በእሷ ላይ ተፅእኖ ከመፍጠርም አልፎ ከላይ የጠቀስነውን ስራዋን (መጽሐፍ 1) ትሰራ ዘንድ ቀስቃሽ ምክንያት ለሆናት ለግንባር ቀደም ፓንአፍሪካኒስቱ፤ የአፍሪካ ፍልስፍናዎች (ኔግሪቲዉድ፣ ኢትዮፒያኒዝም፣ አፍሮፖሊታኒዝም ...) አቀንቃኝና አራማጁ W.E.B. DuBois የ"አመሰግናለሁ" ደብዳቤ የላከችው ድሩሲላ፤ ነጮቹንና ጥቁር ጠል የባለይነት ስሜታቸውን በማዳመር ዘረኝነታቸውን አይን ከሰበከት እያገላበጠች በአጭርና ገላጭ ሐረጋት በመግለፅም አብዝታ ትታወቃለች።

በጥንት አረቢያ፣ ፐርሺያ፣ ባቢሎናዊያን፣ እንዲሁም በህንድ በሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች መካከል አንድነትን በመፍጠር ላይ የተመሰረተው፤ ያ አንድነትም የጥንቱ የኢትዮጵያ ኩሽ ዘር መሆኑ ላይ የሚያተኩረውና በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ጥቁር ህዝቦች በባህል አንድ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርሰው የአፍሪካ-አሜሪካዊቷ ድሩሲላ ታሪክ እንኳን ተጽፎ ተወርቶም የሚያልቅ አይደለም። በመሆኑም ወደ ስራዎቿ እንመለስና በዚህ አምድ፣ በባለውለታነት ትነሳ ዘንድ ወዳስቻላት ስራዋ፤ በስራዋም ተለይታ ትታወቅ ዘንድ ወዳ'በቃት፤ ስመ-ገናናም ወዳ'ደረጋት "መጽሐፍ I" እንመለስ።

ለመሆኑ የምዕራብ ቨርጂኒያ ነዋሪዋ ድሩሲላ ስለ ኢትዮጵያ በሶስት ቅፆች ምን ምን ጉዳዮችን ጻፈች፤ ስለ ምንስ አንስታ ስለ ምንስ ሳታነሳ ቀረች ...? የሚሉት ከሴትየዋ ሁለገብ ሰብእና አኳያ እጅግ ሰፊና ጥልቅ ሲሆኑ፤ ለዛሬ ግን በ1926 ለንባብ ያበቃችውን Wonderful Ethiopians of the Ancient Cushite Empire (ይህ ከሶስቱ የመጀመሪያ ቅጽ በፈጠረው ተጽእኖ ምክንያት ሁለቱ ቅፆች በጉጉት ቢጠበቁም እስካሁን እምጥ ይግቡ ስምጥ የታወቀ ነገር የለም። (በተለይ፣ እራሷ ሂውስተን "ሶስተኛው ቅጽ ከሁሉም የተለየ...." ማለቷን ተከትሎ ሁለቱ ቅፆች የት እንደ ገቡ አለመታወቃቸው አድናቂዎቿን እስከ ዛሬ ከቁጭትና ብስጭት ድባብ ሊያወጣ አልቻለም።)

ድሩሲላ ስለ ኢትዮጵያ ያላለችው ምንም የለም። ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊነት ተንትናለች። የአለሙ ሁሉ መነሻ ስለ መሆኗ አበጥራ በማያነቃንቁ መረጃና ማስረጃዎች በማጠናከር፤ በተዋጣለት የአጻጻፍ ብቃት ፍንትው አድርጋ አሳይታለች። የአለም ሥልጣኔ መነሻ ምንጭ ከየት ተነስቶ የት ድረስ እንደ ዘለቀ አመልክታለች። የኢትዮጵያን ውለታ እኔ ነኝ ባሉ የታሪክ፣ የቲኦሎጂ፣ አርኪኦሎጂ .... ተመራማሪዎች፤ ሳይንቲስቶች .... ጥናቶች፤ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች አስደግፋ ለአለሙ አሳይታለች።

"የአለማችን የክፍለ-ዘመኑ ምርጥ" ሲል ታሪክ የመዘገባት ድሩሲላ ስለ ኢትዮጵያ ያልገለጠችው ምንም እውነት የለም። ያልተናገረችውም አንድም ታሪክ አይገኝም። ለዚህም ነው ይህ ጽሑፍ ርእሱን "ከፈጠሪ በታች፤ ከሰው ሁሉ በላይ ..." ሲል የሰየመው።

ድሩሲላ የኢትዮጵያ ጠላቶች ብዙ መሆናቸውን በግልፅ ተናግራለች። ይህንን የሚያደርጉት ከተራ ግብዝነት ተነስተው መሆኑንም በሚገባቸው ቋንቋ ነግራቸዋለች። መፍትሄው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን አክብሮ፣ አድንቆ፣ እውነቱንም ተቀብሎ (በግድም ቢሆን) መኖር መሆኑን ምንም ወደ ኋላ ሳትል እቅጩን ነግራቸዋለች - የዛሬ 96 አመት። ካፈርኩ አይመልሰኝ ብለው የሚቀጥሉ፤ ልክ እንደ እስከዛሬው ሁሉ አንገቷን አስደፋለሁ ብለው የሚያስቡ ከሆነም እዳው ገብስ እንዳልሆነ፤ ውጤቱም እንሱ እንደሚያስቡት በእነሱ የበላይነት የሚደመደም እንዳልሆነና የመጨረሻው ድል የኢትዮጵያ እንደሚሆን መረጃና ማስረጃዎችን አንድ፣ ሁለት ... በማለት ቆጥራ ታሳያለች - የዛሬ 96 አመት።

እውቁ አለም አቀፍ ምሁር (noted historian and bibliophile) አርተር (ARTHUR A. SCHOMBURG) እጅግ ከመደነቅና ማድነቅም ባለፈ ስራዋ በጣም የተብራራና ሰፊ መሆኑን "illuminating and comprehensive book." በማለት እንደገለፁት የድሩሲላ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎች ከሆነ እኛ ኢትዮጵያዊያን ማንነታችንን በወጉ የማናውቅ ነን፤ በውጪ አካላት ሴራ በቀላሉ ተጠልፈን ለመውደቅ የምንንገዳገድ ግን ደግሞ የማንወድቅ ነን። መከራንና ስቃይን በጥበብ በማሳለፍ ወደ ነበርንብት ሰላማዊ ሁኔታ የምንመለስ ልዩ ሰዎች ነን። እንደ ሌላው ተማርረንና ተስፋ ቆርጠን አገራችንን ለውድቀት አሳልፈን የምንሰጥ፤ ስደትን መምርጫችን የምናደርግ አይደለንም። አዛኝ፣ ሩህሩህ ነን፣ አትንኩኝ ባይም ነን። የግዛት ወሰናችን ከአፍሪካም አልፎ እስከ ስፔን ድረስ ሁሉ ዘልቆ የነበረ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በንግድ እንቅስቃሴዋ (ከህንድ ውቅያኖስ ዳርቻዎች እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ጠረፎች) የመሪነት ሚናን ስትጫወት፤ የተከበሩ ማእድናትን ለአለም ገበያ ስታቀርብ፤ በኪነ-ህንፃ ፊት መሪ የነበረች ("በዳቦድና በዳካ የሚታዩት ቤተመቅደሶች የተገነቡት በኢትዮጵያዊው ንጉስ ኤርጋሜነስ ዘመን ነው" ያለች ሲሆን፤ ይህም ከብዙ ማሳያዎቿ አንዱ ነው) ... አገር ነች።

ስለ ኢትዮጵያ እውነቱን ለማወቅና ትክክለኛ የህሊና ዳኝነት ለመስጠት የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ከዘመናችን መጻሕፍት አጥጋቢ መረጃዎች ሊያገኙ ያልቻሉበት ዋናው ምክንያት ፊታቸውን ወደ ጥንታዊያኑ ያረጁና ያፈጁ መዛግብትና ማህደራት ያለማዞራቸው ሲሆን፤ ወደ ጥንቱ መጻሕፍት ፊታቸውን መልሰው ቢሆንና ለጥቅም ባይገዙ ኖሮ ተዝቆ የማያበቃ የምስክርነት ማስረጃዎችን ባገኙ ነበር (ፒራሚድ ገንቢዎቹ ...፣ ገጽ 53)። ዳሩ ምን ያደርጋል፣ የአሁኑ ዘመን ጸሐፊዎች ለጥቅም ያደሩ በመሆናቸው እውነቱን ፈልፍሎ ለማውጣት አይችሉም ... የምትለው ድሩሲላ፣ ኢትዮጵያዊያንን በወታደራዊ ጀብድ የሚችላቸው አልነበረም፤ የተዋጣላቸው መርከበኞች ነበሩ፤ በግብርናው፣ ባህላዊ ህክምናው፣ ኬሚስትሪና ፊዚክሱ ... አለምን ያሰለጠኑ ሲሆን፤ የሥነጽሑፍ ተጽእኗቸው አለም አቀፍ ነው። በሥነፊደል፣ በቀለም ስራ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ድል በማድረግ፣ ለአገር በመሞት ... የሚደርስባቸው የለም።

ይህንን መጽሐፍ የጻፍኩት (አላማው) ኢትዮጵያዊያንን ለማግነን፤ ወይም እነሱ ኩራት እንዲሰማቸውና እንዲኩራሩ ሳይሆን ያለፈ ማንነታቸውን አውቀው፣ አያት ቅድመ አያቶቻቸው የሰሩትን ተገንዝበው የበለጠ እንዲሰሩ ማድረግ ነው የምትለው ድሩሲላ መሸንቆጧንም አልተወችም። በ"Wonderful Ethiopians of the Ancient Cushite Empire" ላይ እንደሰፈረው፤

እኛ ኢትዮጵያዊያን ታሪክን መርምረን እራሳችንን ለማወቅ የማንጥር፤ አያት ቅድመ አያቶቻችን ምን ምን ሰርተው እንዳለፉ ለማወቅ ምንም ደንታ እንኳን የሌለን፤ ከአለሙ ሁሉ በላይ፣ የአለሙ አይን ገላጭ ሆነን እያለ አንዱን እንኳን ለአለም እንዳላበረከተ ሁሉ የራሳችንን መልሰን ከሰው ፈላጊ ሆነን የቀረን ነን፤ ወታደራዊ ጀግንነታችን የት ድረስ እንደነበር እንኳን ለማወቅ ምንም ጥረት የማናደርግ .....፤ ግን ደግሞ እግዚአብሔር አብዝቶ የሚወደንና እሚጠብቀን ሰዎች ነን - እንደ አፍሪካ-አሜሪካዊቷ ድሩሲላ ዱንጂ ሂውስተን ጥልቅ ምርምርና ጥናት።

ዛሬ የናቅናቸው ኢትዮጵያዊያን ዘመናት ያሳለፉትን የግብፅ ፒራሚዶች የገነቡ፣ አፈራቸው ግብፅን ያለማ፣ የኮሚዩኒኬሽን ሥርዓትን በመዘርጋት የታወቁ፣ የስልጣኔን መሰረት ያስቀመጡ ህዝቦች ለመሆናቸው አይነ ልቦናችንን ከፍተን የግድ መቀበል ያለብን ጉዳይ ነው የምትለው ድሩሲላ፣ የከላውዴዊያኑ ጥንታዊ ባህል ከጥንታዊው ኩሽ የኢትዮጵያ ኢምፓየር የተገኘ፤ የሁሉም ነገር መነሻ አባይና ዳርቻው ነውም ነው የምትለው።

ኃያል ነን ባዮቹና የእንግሊዝ፣ ጀርመን፣ አሜሪካ ... ሕዝቦች በሌላው ላይ ተፅእኖ ለማድረስ የሚሞክሩት፤ በደልም የሚፈፅሙት ታሪክን ባለማወቃቸው፤ ግብዝነታቸው ነው የምትለው ድሩሲላ እኛ እውነቱን ብንገልፅ ይማራሉ፤ ችግሩም ይወገዳል ስትልም መፍትሄውን ታስቀምጣለች።

ድሩሲላ ስራዎቿን በማይነቃነቁ መሰረቶች ላይ መትከሏ የነቃፊዎቿን ልሳን ለመዘጋት እጅጉን ጠቅሟታል። ሄሮዱተስን ጨምሮ፣ ስራዋን ሰር ኤች ጆንሰን እንዳለው ...፣ በንሰን እንደፃፈውና ራውሊንሰን እንዳረጋገጠው ...፣ የኤሊየት ስሚዝን ጥናትና ምርምር ተመርኩዞ ዌልስ እንደ መሰከረው ...፣ በሳንስክሪት ሰፍሮ እንደሚገኘው ... በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ምእራፍ .... ላይ እንደሚነበበው...፣ ሂረን በምርምር ስራው እንደደረሰበት...፣ እንደ የፕቶሎሚያክ ጸሐፍት አገላለፅ ...፣ በሳይክሎፔዲያ ኦፍ ቢቢሊካል ሊተሬቸር ላይ እንደ ሰፈረው ...፣ ባልድዊን ዳዩዶረስን ጠቅሶ እንደፃፈው ...፣ ሶሎንም ሆነ ፕሌቶ ይህን የተቀበሉት ...፣ ኒብሁር እንደሚለው ...፣ እንደ ሬክሉስ አገላለፅ ...፣ ሳይስ ባገኘው መረጃ መሰረት ...፣ ዶነሊ እንዳረጋገጠው ...፣ እንደ ደ ሩዥ አስተሳሰብ ...፣ አልደንድሮፐ .... ሲል ጽፏል፤ Duncker-History of Antiquity በተባለው መጽሐፍ (ቅፅ 1) ላይ እንደሰፈረው ...፣ አሜሊያ ቢ ኤድዋርድስ A Thousand Miles Up The Nile በተባለው መጽሐፏ ላይ እንዳሰፈረችው ....፣ ሰር ጂ ጋርድነር በ.... መጽሐፉ ላይ እንዳሰፈረው ... እና ሌሎች በርካታ በአለማችን "አንቱ" የተባሉ ምንጮችን ተጠቅማለች። ይህም ስራዋ ምእተ አመትን አስቆጥሮ እንኳን ተፈላጊነቱ ሳይቀንስ እንዲዘልቅ አድርጎታል።

በመጨረሻም፣ አፍሪካ-አሜሪካዊቷ ድሩሲላ ዱንጂ ሂውስተን ስራዋን በሚገባ ሰርታ፤ ስለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን እውነቱን ተናግራ ወደ'ማይቀረው ሄዳለች። ስራዎቿም በአለም የመጻሕፍት ደብራት ሁሉ ነግሰዋል (ከኢትዮጵያ ውስጥ በስተቀር)። ወደ ፊት ከዚህ ከዛሬው በተሻለ እናስታውሳታለን፤ ስራዎቿም በየቤተመጻሕፍቶቻችን ይቀመጣሉ ብለን እናስባለን። ለዛሬው፤ "ነፍሷን በገነት ያኑርልን" እያልን እንሰናበታለን።



ድሩሲላ ዱንጂ ሂውስተን
(ጃንዋሪ 20, 1876 1876 - ፌብሯሪ 8, 1941 1941)

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ሉሲዎቹ በሴካፋ ግማሽ ፍጻሜ ዩጋንዳን ይገጥማሉ

**ቦጋለ አበበ**

በዩጋንዳ አስተናጋጅነት ስምንት አገራት በሁለት ምድብ ተከፍለው የተፋለሙበት የመካከለኛውና ምሥራቅ አፍሪካ(ሴካፋ) የሴቶች ዋንጫ የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚዎች ተለይተዋል። በውድድሩ እየተካፈለ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሴቶች ብሔራዊ ቡድን(ሉሲዎቹ) ከሶስት ጨዋታ በኋላ የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ ከሆኑ አራት አገራት አንዱ መሆን ችሏል።

የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ዛንዚባርን አምስት ለምንም በሆነ ሰፊ ውጤት ማሸነፍ የቻሉት ሉሲዎቹ፣ የምድባቸውን ሁለተኛ ጨዋታ ባለፈው ቅዳሜ ከታንዛኒያ ጋር በማድረግ ሁለት ለሁለት በሆነ አቻ ውጤት ማጠናቀቃቸው ይታወሳል። ሉሲዎቹ የምድባቸውን ሶስተኛና የመጨረሻ ጨዋታ ከትናንት በስቲያ ደቡብ ሱዳንን በመግጠም አራት ለዜሮ ማሸነፋቸውን ተከትሎም የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ መሆን ችለዋል። ሉሲዎቹ ከምድባቸው ሰባት ነጥብና ዘጠኝ ግብ ይዘው ሁለተኛ በመሆን የግማሽ ፍጻሜውን ፍልሚያ የተቀላቀሉ ሲሆን፣ በዚሁ ምድብ የምትገኘው ታንዛኒያ ሶስተኛውን ጨዋታ ዛንዚባርን በአንድ ደርዘን ግብ አስራ ሁለት ለዜሮ በመርታቷ በግብ ክፍያ በልጣ ከምድቡ አንደኛ በመሆን ግማሽ ፍጻሜውን ልትቀላቀል ችላለች። በዚህም ሉሲዎቹ በሌላኛው ምድብ አንደኛ ሆና ያጠናቀቀችው የውድድሩ አስተናጋጅና ጠንካራ ቡድን ያላትን ዩጋንዳን በግማሽ ፍጻሜ የሚገጥሙ ይሆናል።

የምድብ ጨዋታዎቿን ሙሉ በሙሉ ማሸነፍ የቻለችው ዩጋንዳ በተለይም የመጨረሻውን የምድብ ጨዋታ ቡሩንዲን



አረጋሽ ካልሳ ደቡብ ሱዳን ላይ ሶስት ግቦችን በማስቆጠር የጨዋታው ኮከብ ሆና ተመርጣለች፣

ሶስት ለአንድ መርታቷ የሚታወስ ሲሆን ቡሩንዲ ሁለት ጨዋታዎችን በማሸነፏ የግማሽ ፍጻሜ ፍልሚያውን ተቀላቅላ ያለፈው ውድድር የፍጻሜ ተፋላሚዋ ታንዛኒያን የምትገጥም ይሆናል።

በሶስቱ የምድብ ጨዋታዎች አምስት ግቦችን ከመረብ ያሳረፈችው የታንዛኒያዋ ተጫዋች አፓህ ክሌመንት የኮከብ ግብ አግቢነቱን ፉክክር በቀዳሚነት ትመራለች። ከደቡብ ሱዳን ጋር በነበረው ጨዋታ ሶስት ግቦችን ለሉሲዎቹ ማስቆጠር የቻለችው አረጋሽ ካልሳ እንዲሁም በሶስቱ ጨዋታዎች ግቦችን ማስቆጠር የቻለችው የሉሲዎቹ ወሳኝ የአጥቂ መስመር ተጫዋች ሎዛ አበራ አራት አራት ግቦችን በማስቆጠር የኮከብ ግብ አግቢነቱን ፉክክር በቅርብ ርቀት ይከተላሉ።

ዩጋንዳ ለአምስተኛ ጊዜ እያስተናገደች በሚገኘው የሴካፋ ውድድር የፍጻሜ ተፋላሚ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁ አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነች። ይህንን ለማሳካት ግን ከአዘጋጇ ዩጋንዳ የግማሽ ፍጻሜ ጠንካራ ፉክክር ይጠብቃታል። አዲሱ የሉሲዎቹ አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል ከበርካታ ወራት በፊት በሴካፋ ከ20 ዓመት በታች ውድድር የሉሲዎቹን ተተኪዎች እየመራ የውድድሩ አዘጋጅ የነበረችውን ዩጋንዳን በፍጻሜ ጨዋታ ከመመራት ተነስቶ ሶስት ለሁለት በማሸነፍ ሻምፒዮን መሆኑ ይታወሳል። ከዋናው ብሔራዊ ቡድን ጋርም ዩጋንዳ የውድድሩ አዘጋጅ ሆና በግማሽ ፍጻሜ ተገናኝተዋል።

አሰልጣኝ ፍሬው ከ20 ዓመት በታች የሴካፋን ዋንጫ ከስኬታማው የወጣቶች ቡድን ጋር ሲያነሱ በኢትዮጵያ ሴቶች እግር ኳስ ታሪክ ትልቅ ስኬት ሆኖ ተመዝግቧል። ከሴካፋው ጣፋጭ ድል በኋላም ያንኑ ቡድን እየመሩ በዓለም ከ20 ዓመት በታች ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታ እስከ መጨረሻውና አራተኛው ዙር መጓዛቸው ይታወሳል።

አሰልጣኙ በወጣቶች ቡድን ያስመዘገቡት ውጤት በዋናው ብሔራዊ ቡድንም ተመሳሳይ ስኬት ለማስመዝገብ ተስፋ እንዲጣልባቸው አድርጓል። ለዚህም ከሳምንታት በፊት ሉሲዎቹን በዋና አሰልጣኝነት ለመምራት ኃላፊነቱ ሲሰጣቸው የቡድን ስብስባቸውን ስኬታማ ከነበረው የ20 ዓመት በታች ቡድን በርካታ ወጣት ተጫዋቾችን በማሳደግ ከነባሮቹና ልምድ ካካበቱት ጋር በማጣመር ሲዘጋጁ ቆይተዋል። ሉሲዎቹ ከዩጋንዳ ጋር በሚኖረው የግማሽ ፍጻሜ ፍልሚያ አሸንፈው ለፍጻሜ መድረስ ከቻሉ ለአሰልጣኙም ይሁን ለብሔራዊ ቡድኑ በውድድሩ ታሪክ ትልቅ ስኬት ሆኖ ይመዘገባል። ኢትዮጵያ ባለፉት አራት የሴካፋ ዋንጫዎች እኤአ በ2016 እና 2018 ዩጋንዳና ሩዋንዳ ላይ በተዘጋጀው ውድድር ሶስተኛ ሆና ያጠናቀቀችበት ታሪክ ትልቁ ውጤት ሆኖ ይታወሳል። አሰልጣኝ ፍሬውና ሉሲዎቹ ከዩጋንዳው የግማሽ ፍጻሜ ፍልሚያ በኋላ ይህን ታሪክ የማሻሻል ወይም የመጋራት እድሉ በእጃቸው ይገኛል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## በአገሪቱ የትርጉም ሥራ ያለበትን ገመና የገለጠው ጉባኤ

**ሶሎሞን በየነ**

የትርጉምና የአስተርጓሚነት ሙያ በአገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተግባቦት፣ ለንግድ መሳለጥ፣ ለጤናው ዘርፍ ውጤታማነት፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ሆኖም የትርጉም ሥራ በአገሪቱ ለረጅም ጊዜ ሲሠራበት ቢቆይም፤ ዘርፉን በበላይነት የሚመራና የሚያስተዳድር ተቋም ባለመኖሩ ሙያው ዘመኑን በሚመጥን መልኩ እንዳለማና እንዳላደገ ምሁራን ሲናገሩ ይደመጣሉ።

ከዚህ አኳያ የትርጉምና የአስተርጓሚነት ሙያን ለማሳደግ የሚያስችል አስፈላጊው ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲፈጠር በ2012 ዓ.ም በጸደቀው የቋንቋ ፖሊሲ በግልጽ ተቀምጧል። ባህልና ስፖርት ሚኒስቴርም ዘርፉን በበላይነት የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀቱን ተግባራዊ ለማድረግ አጠቃላይ አገራዊ ዳሰሳዊ ጥናት በማድረግ፣ ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር እና ከስምንት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር የትርጉምና አስተርጓሚነት ሙያን ለማዳበርና የሰው ኃይል ለመፍራት የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጅቷል።

ከዚህ ባሻገር በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን አገራዊ የትርጉምና አስተርጓሚነት ጉባኤን ሚኒስቴሩ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ባለፈው ዓመት በአርባ ምንጭ ከተማ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ሁለተኛው አገራዊ የትርጉም ጉባኤ" translation for national consensus (ትርጉም ለአገራዊ መግባባት)" በሚል መሪቃል በአዳማ ከተማ ከትናንት ሰሞኑን ለሁለት ቀናት ተካሂዷል።

በጉባኤው የመክፈቻ ንግግር ያደርጉት በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የባህልና የቋንቋ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ወርቅነሽ ብሩ እንደገለጹት፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔርና ብሔረሰቦች መኖሪያ የእምቅ ድንቃ ድንቅ ባህላዊ እሴትና የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት ናት። እነዚህ ቋንቋዎች በተለያዩ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ 53ቱ ፊደል ተቀርጾላቸው የመማሪያ ቋንቋ ሆነዋል።

ቋንቋ የባህልና የማንነት መገለጫ ከመሆኑም ባሻገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ፋይዳው በርካታ በመሆኑ በጥናት ላይ ተመስርቶ ቋንቋን ማልማትና ማሳደግ ያስፈልጋል። ስለዚህ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 39 (2) ላይ ማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል። ይህንን መነሻ በማድረግ ቋንቋዎች የያዟቸውን የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶች፣ እሴቶች እና አስተሳሰቦች ከአንዱ ወደ ሌሎች ለማስተላለፍ ትርጉምና አስተርጓሚነት ሙያ ልማት ላይ እየተሠራ ይገኛል።

ስለዚህ የጉባኤው ዋና አላማ በትርጉምና አስተርጓሚነት ሙያ ዙሪያ ጠንካራ ውይይት በማድረግ ሙያው ለአገራዊ አንድነትና መግባባት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ለይቶ በማውጣት ለመንግስት ፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ሀሳብ ለማሰባሰብ ያስችላል ብለዋል።

"ይህንን አገራዊ ጉባኤ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር መካሄዱ ለቋንቋዎቻችን እድገትና ለሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ አለው" ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታዋ ጠቁመው፤ ጉባኤው የትርጉምና አስተርጓሚነት ሙያን ለማልማት በመዋቅር፣ በአደረጃጀትና በስትራቴጂ የሚመራበትን አቅጣጫ ለማመላከት ይረዳል። እንዲሁም በቋንቋዎች የሚገኙ ዘርፈ ብዙ የመረጃ ሀብቶችን ለአገር ሁለንተናዊ ልማት ያላቸውን ፋይዳ ለማስገንዘብና ለጥናትና ምርምር ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድርግ ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ተሾመ አብዶ (ዶክተር) በበኩላቸው፤ በዓለማችን ላይ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ቋንቋዎች የሚነገር ሲሆን፤ አንደኛው የሌላኛውን ቋንቋ በመማር ወይም በማስተርጎም ከሌላ ማህበረሰብ ጋር ያለምንም ችግር ሲኖር ይስተዋላል። በአገራችንም ከ80 በላይ ቋንቋዎች የሚነገር ሲሆን፤ አንዱ የሌላውን ቋንቋ በመማር ወይም በማስተርጎም ለዘመናት ተከባብረው አብሮ በመኖር ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም ብሔራዊ መግባባትን ከምናሳካባቸው አንዱ የተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎችን ሰዎች በቀላሉ መረዳት ወይም ማወቅ እንዲችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ነው። ምክንያቱም አንዱ ማህበረሰብ የሌላውን ቋንቋ ለመማር በሚያደርገው ጥረት ውስጥ በተመሳሳይ አንዱ የሌላውን ባህልና እሴት ስለሚማርና ማወቅ ስለሚችል ለብሔራዊ መግባባቱ ምቹ መደላድል ይፈጥራል። ስለዚህ ይህ አገራዊ ገባኤ የትርጉምና የአስተርጓሚነት ሙያን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማልማትና አገራዊ መግባባት ለማስፈን የማይተካ ሚና እንዳለው ገልጸዋል።

በጉባኤው "የትርጉም ሙያዊነት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ በየነ እንደገለጹት፤ የትርጉም ሥራ በሀገሪቱ ለረጅም ጊዜ ሲሠራበት ቆይቷል። ሆኖም ግን በአገሪቱ የትርጉም ጥራት የሚለካና ዘርፉን የሚቆጣጠር ተቋም ባለመኖሩ የትርጉም ሥራዎች ጥራታቸው የወረደ መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ የትርጉም ሥራ ዕልፍ ዘመን ቢያስቆጥርም ሙያው ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት በዲግሪ፣ በማስተርስ ወይም በዶክትሬት ዲግሪ እየተሰጠ አይደለም። በዚህም በሀገሪቱ የትርጉም ሥራ በሳይንሳዊ መንገድ ሳይሆን በዘልማድ እየተሠራ ይገኛል። ስለዚህ የትርጉም ሥራን በበላይነት የሚመራ፣ የሚያስተዳድር እንዲሁም የሚቆጣጠር ተቋም ባለመኖሩ ብዙዎቹ የትርጉም ሥራዎች ክፍተትና ስህተት አለባቸው። ጥራት ባለው ደረጃ አይደለም እየተሠራ ያለው፡፡

በተጨማሪም የማስተማሪያ መጽሐፍት ቀጥታ ከእንግሊዘኛ ወይም ከሌሎች ቋንቋዎች ወደ አገሪቱ መማሪያ ቋንቋዎች ተተርጉመው ነው ለተማሪዎች እየቀረቡ የሚገኙት። ስለዚህ የትርጉም ሥራ ጥራት መጓደሉ በትውልድ ላይ ለመግባባት እንከን ሲፈጥር ይስተዋላል። ሌላው የፖለቲካ ወይም የፖሊሲ ሰነዶች ጥራት ባለው ደረጃ ካልተተረጎሙ በአገር ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ከባድ ነው። ይህ ክፍተት ደግሞ አለመረዳዳትን ይፈጥራል። አለመረዳዳት ደግሞ እንደአገር አለመግባባትን ይፈጥራል ብለዋል።

በገጽ፣ በቃላት፣ በጥራዝና በመሳሰሉት የትርጉም ሥራዎችን የሚያስከፍሉ የትርጉም ድርጅቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ መስፈርት ስለሌለ የማስተርጎሚያ ዋጋ የዋዠቀና የተለያየ ነው። ወጥነትም የለውም። ስለዚህ የትርጉም ሥራን በበላይነት የሚመራ ተቋም ቢኖር ባለሙያው ትክክለኛ የሥራውን ዋጋ እንዲያገኝ በአንጻሩ ደግሞ ተገልጋዩ ማኅበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያስችላል ብለዋል።

በጥቅሉ የትርጉም ሥራን በበላይነት የሚያስተዳድር ተቋም ቢቋቋም የባለሙያውን የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፤ የሚሠሩ የትርጉም ሥራዎች ጥራትም ይከታተላል፡፡ እንዲሁም በየትኛውም ቦታ ለሚሠሩ የትርጉም ሥራዎች መመዘኛ መስፈርት በማውጣት ወጥነትና ጥራት ያለው ሥራ እንዲሠራና የአስተርጓሚዎች ማኅበራት ለማቋቋም ይረዳል። ከዚህ ባለፈ በቀጣይነት እና በዘላቂነት ለባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠትና ዘርፉን ለማልማት ያስችላል። ስለዚህ መንግሥት የተቋሙ መቋቋም ያለውን ፋይዳ ከግምት በማስገባት ተቋሙን በማቋቋም ድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ረዳት ፕሮፌሰሩ አሳስበዋል።

በጉባኤው የትርጉምና የአስተርጓሚነት ሙያ ሳይንሳዊና ተጨባጭ እውነታዎች ምንድ ናቸው? የትርጉምና የአስተርጓሚነት ሥራ በአገሪቱ ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል? በአገሪቱ ከምልክት ቋንቋዎች አኳያስ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚሉ ይዘቶችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism
Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia